# ኢፕድ አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 137 ጥር 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ እንደገለጹት፡-

## - መምህራን ያነሷቸው ጥያቄዎች በሂደት መልስ እንዲያገኙ ይደረጋል
## - ምሁራን ከሰፈር ፖለቲካ ወጥተው ሀገራዊ ዕይታቸውን ሊያሰፉ ይገባል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- መምህራን ያነሷቸውን ጥያቄዎች በመለየት በሂደት ተገቢውን መልስ እንዲያገኙ ይደረጋል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ። ምሁራን ለሀገራቸው ያላቸውን አበርክቶ ለማሳደግም ከሰፈር ፖለቲካ ወጥተው ሀገራዊ ዕይታቸውን ሊያሰፉ ይገባል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ምሁራን ጋር በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ትናንት ውይይት አድርገዋል። በወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ምሁራኑ የደመወዝ፣ የጥቅማጥቅምና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ ጥያቄ አቅርበዋል። በተጨማሪ ከሀገሪቷ የጸጥታ ሁኔታ፣ ለትምህርት ጥራት ከሚያግዙ ጉዳዮች፣ ስለአካል ጉዳተኞችና የሴቶች



ተሳትፎ፣ ጉዳት ስለደረሰባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ድጋፍ በተመለከተ እንዲሁም ከሀገራዊ አንድነት ጋር የተቆራኙ ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በምላሻቸው፤ ምሁራን ለሀገር ግንባታ ትልቅ አቅም መሆናቸውን አንስተው፤ ከደመወዝ ጥቅማጥቅምና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎችን በሂደት የሚፈቱበት መንገድ እንዳለ አመላክተዋል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በራሳቸው የኢኮኖሚ አቅም እንዲተዳደሩ ማድረግ የዩኒቨርሲቲ ማኅበረሰብን ኢኮኖሚያዊ አቅም በዘለቄታዊነት ማጠናከር የሚረዳ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመዋል።

ራስ ገዝ ይሁኑ ማለት ግን መንግስት ለዩኒቨርሲቲዎች በጀት አይመድብም ማለት አይደለም ያሉት ዶክተር ዐቢይ፤ ከአሁኑ በበለጠ በጀት በመመደብ የምርምር ስራዎች የሚደገፍበት ዕድልም እንዳለ ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ኮሎኔል ጥላሁን ደምሴ

## በብሔራዊ ደህንነት ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት ተካሄደ

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነት እና በወቅታዊና ዓለም አቀፋዊ ጂኦፖለቲካዊ ደህንነት ላይ ያተኮረ የፓናል ውይይት በኢፌዴሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ አዘጋጅነት ተካሄደ።

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ የትምህርትና ሥልጠና ዲፓርትመንት ዲን ኮሎኔል ጥላሁን ደምሴ

በብሔራዊ ደህንነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

## የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚኒስትሮችን ሹመት አፀደቀ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚኒስትሮችን ሹመት አጽድቋል፡፡ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅን ጨምሮ የጋራ የሕግ ትብብር፣ የአሳልፎ መስጠት ስምምነቶችንና ደንቦችን መርምሮ ለዝርዝር ዕይታ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፡፡

ስድስተኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በትናንትናው ዕለት ባደረገው ሁለተኛ ዓመት የስራ ዘመን ስምንተኛ መደበኛ ስብሰባው የቀረበለትን የሚኒስትሮች ሹመት አጸድቋል፡፡ በዚህም መሰረት ዶክተር አለሙ ስሜ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር፣ ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ የማዕድን ሚኒስትር፣ እንዲሁም ዶክተር ግርማ አመንቴ የግብርና ሚኒስትር ሆነው በምክር ቤቱ በአብላጫ ድምጽ ሹመታቸው ጸድቋል።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ከፍተኛ አመራሮች ከኅብረተሰቡ ጋር በወለጋ ያደረጉት ውይይት ውጤታማ መሆኑ ተገለጸ

ገጽ 4


ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል::
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia






# የሆቴል ዘርፉን ይበልጥ ለማነቃቃት ለአገልግሎት ሰጪዎች ስልጠና ይሰጣል

- ዶክተር ሂሩት ካሳው

ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ ፡- የሆቴል ዘርፉን ይበልጥ ለማነቃቃት ለሆቴልና ሆስፒታሊቲ አገልግሎት ሰጪዎች ከያዝነው ዓመት ጀምሮ ስልጠና እንደሚሰጥ የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ገለጸ፡፡

እንደሀገር ባለፉት አራት ዓመታት በነበረው ሀገራዊ ሁኔታ ተንተርሰው ገንዘባቸውን ከማሸሽ ተቆጥበው በሀገራቸው የሆቴልና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ልማት ላይ ያዋሉ ባለሀብቶች እንደሚመሰገኑ ተነግሯል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ-ጥበብና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ሂሩት ካሳው እንደተናገሩት፤ የሆቴል ዘርፉን ለማሳደግ ስልጠና መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ይህንን መሰረት በማድረግም በዘርፉ ለተሰማሩ ባለሀብቶችና ባለሙያዎች ስልጠናዎችን ከያዝነው በጀት ዓመት ጀምሮ ለመስጠት ታቅዶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡

እንደ ዶክተር ሂሩት ገለጻ፣ በቀጣይ በመዲናዋ ላሉት የሆቴልና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶችና ባለሙያዎች የሚሰጠው ስልጠናም የዘርፉን ችግሮች ለመቅረፍ ከሚደረጉ ጥረቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሳደግም የሚረዳ ነው ብለዋል፡፡

የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ በበኩላቸው፣ ባለፉት አራት ዓመታት የቱሪዝም ዘርፉ በብዙ ነገሮች ተፈትኗል ነው ያሉት፡፡

እንደ ሀገር የቱሪዝም ዘርፍ በኮሮና ወረርሽኝና መሰል ፈተናዎች በተጨማሪ ከውጪና በሀገር ውስጥ የገጠሙት ፈተናዎችን ተቋቁሞ አልፏል ያሉት አቶ ስለሺ፤ በሀገር ውስጥ ያሉት ባለሀብቶች፣ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ገንዘባቸውን ከማሸሽ ይልቅ በዘርፍ ልማት ላይ አውለዋል፡፡

በመሆኑም ዜጎች በሁኔታዎች ሳይደናገጡና ለሀገራቸው ልማት ቅድሚያ በመስጠት መዋዕለ ነዋያቸውን በሀገራቸው ያፈሰሱ ባለሀብቶች ገንዘባቸውን ከማሸሽ ይልቅ በሆቴልና ሆስፒታሊቲ ዘርፍ ልማት በማዋላቸው ሊመሰገኑ ይገባል፣ በቀጣይም በርትተው እንዲሰሩ በመንግስት በኩል የሚደረገው የድጋፍ ስራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡


ዶክተር ሂሩት ካሳው


አቶ ስለሺ ግርማ

# ቢሮው በግማሽ በጀት ዓመት የዕቅዱን 107 በመቶ ገቢ መሰብሰቡን አስታወቀ

## በ260 ባለሙያዎችና አመራሮች ላይ አስተዳደራዊ ርምጃ ተወስዷል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- በግማሽ በጀት ዓመቱ 42 ነጥብ 29 ቢሊየን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 107 በመቶ መሰብሰቡን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ። ከ2014 በጀት ጀምሮ እስከ ባለፉት ስድስት ወራት በ260 ባለሙያዎችና አመራሮች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ የ2015 በጀት የግማሽ በጀት ዓመት የስራ አፈጻጸምን በማስመልከት በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ ቢሮው በከተማ አስተዳደሩ የተጣለበትን ገቢ የመሰብሰብ ኃላፊነት ለመወጣት፣ ከተማዋ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ በበጀት ዓመቱ የ70 ቢሊየን ብር ዕቅድን ለማሳካት ባለፉት ስድስት ወራት ቅንጅታዊ አሰራሮችን አከናውኗል።

ቢሮው ባለፉት ስድስት ወራት የግብር ከፋዮቹን ቁጥር ወደ 70 ሺህ ያሳደገ ሲሆን ፤ ከባለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ15 ነጥብ 1 በመቶ ዕድገት አለው። የስድስት ወራት የገቢ ዕቅድ እንዲሳካ በሞደርናይዜሽን፣ በታክስና በህግ ዘርፎች የቅንጅት ስራዎች ማከናወናቸውን አቶ ሙሉጌታ ገልጸዋል።

የበጀት ዓመቱን የገቢ ዕቅድ ለማሳካት ከአጋርና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በጋራ በመንቀሳቀስ፣ የግብር ክፍያን የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን የሲ.ቢ.ኢ፣ የቴሌ ብርና የ7075 የውስጥ የስልክ መስመሮችን እንዲጠቀም በማድረግ ፈጣን መስተንግዶ እየተሰጠ መሆኑን አቶ ሙሉጌታ ተናግረዋል።

የቢሮ ኃላፊው፤ ገቢው ከታክስ፣ ከማዘጋጃ ቤታዊ ፣ ቀጥታ ታክስና ቀጥታ ካልሆነ ታክስ በስድስት ወራት የተሰበሰበ ሲሆን፤ በዓመቱ ሊሰበሰብ ከታቀደው 70 ቢሊየን ብር ጋር ሲነነፃፀር 60 በመቶ ተከናውኗል። ይህም በስድስት ወራት ውስጥ ተቋሙ ከያዘው ዕቅድ አንፃር 107 በመቶ ነው። ለገቢው መሰብሰብ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ባህል መዳበሩና ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩ


አቶ ሙሉጌታ ተፈራ

አስተዋጽኦ አለው። ቢሮው ይህንን ገንዘብ መሰብሰብ የቻለው ከ449 ሺህ 816 ግብር ከፋዮች መሆኑን የቢሮው ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተረፈ ተናግረዋል።

ከ2014 ጀምሮ በ260 ባለሙያዎችና አመራሮች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዷል። በተጨማሪም ግብር በማጭበርበር፣ በመሰወርና በሌላ ወንጀል የተያዙ አንድ ሺ ነጋዴዎች ላይ ርምጃ ተወስዷል።

አቶ ሙሉጌታ ቢሮው ከዓመት ዓመት በግብር አሰባሰቡ እየተሻሻለ ቢሆንም የሀሰተኛ ደረሰኝ ችግር በመሠረታዊነት አለመፈታቱ፣ ያለደረሰኝ አገልግሎትና ዕቃ መሸጥ፣ ወይም ከዋጋ አሳንሶ መሸጥ ተግዳሮቶች ሲሆኑ፤ ችግሩን ለመፍታት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ማልማት፣ የኢ-መደበኛ ንግድ አሰራር ጥናቶች ወደ ተግባር ማስገባትና አሰራር አድርጎ ማስቀጠል ይጠበቃል ብለዋል።

# ተቋሙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶችን ሚና ከፍ ለማድረግ እንደሚሰራ ገለጸ

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚጫወቱትን ሀገራዊ ሚና ከፍ ለማድረግ እንደሚሠራ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን በትናንትናው ዕለት ባከናወነው የ2015 በጀት ዓመት የስድስት ወራት እቅድ አፈጻጸም ላይ የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አቶ ጂማ ዲልቦ እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ እንዲሁም የፌዴራል እና የክልል ባለድርሻ አካላት ጋር የተጀመሩ አባላትን የመመዝገብ፣ እውቅና የመስጠት እንዲሁም የድጋፍና ክትትል ስራዎችን በማጠናከር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የተሻለ አሰራር እንዲኖር እየሰራ ነው፡፡


አቶ ጂማ ዲልቦ

አቶ ጂማ በግማሽ ዓመቱ ባለስልጣኑ ከውስጥ ከአደረጃጀት ጀምሮ የመደራጀት መብትን በማስከበር እና የኅብረተሰቡን የላቀ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የድጋፍና ክትትል ስራዎች፣ የበጎ ፍቃድ ስራ፣ ጥራትን የጠበቀ እና የተቀላጠፈ አገልግሎት ተሰርቷል ብለዋል፡፡ ስትራቴጂክ እቅዱን ተግባራዊ ባደረገ መልኩ እና እቅዱን ማስፈጸም የሚያስችል አዲስ አደረጃጀት እና መዋቅር ተጠንቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን የስትራቴጂክ ጉዳዮች ስራ አስፈጻሚ ወ/ሮ ቃልኪዳን መንግስቴ በበኩላቸው፤ በስድስት ወራት ውስጥ ከመደራጀት መብት መረጋገጥ ጋር በተያያዘ 426 አዲስ ድርጅቶችን ለመመዝገብ ታቅዶ 299 ሀገር በቀል እና 27 የውጭ በአጠቃላይ 326 ድርጅቶች ተመዝግበዋል ብለዋል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ህግ ጋር በተያያዘ ሁሉም ክልሎች ተቀራራቢ የሆነ የህግ ማዕቀፍ እንዲያወጡ እና የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት ድጋፍ እና ቅንጅት ተደርጓል፡፡ ከአጋር አካላት ጋር በጋራ በጦርነት እና በድርቅ ለተጎዱ ድጋፍ ለማሰባሰብ የምግብና ቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም የተለያዩ የበጎ ፍቃድ ስራዎችን ተሰርቷል ሲሉ ወ/ሮ ቃልኪዳን ገልጸዋል፡፡


ወ/ሮ ቃልኪዳን መንግስቴ

በግማሽ በጀት ዓመቱ ላይ የታዩ ጥንካሬዎችን በማጠናከር እና ተግዳሮቶችን እና ድክመቶችን በማሻሻል ለመስራት ከአጋር አካላት ጋር ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ዜና

# 40 የዲያስፖራ አባላት እውቅና ሊሰጣቸው ነው

**እፀገነት አክሊሉ**

አዲስ አበባ፡- ሀገር ሊያድግ የሚችለው እውቀትና ቴክኖሎጂን በማሸጋገር በሀገር ቤት ያሉ ተቋማትን አቅም ለመገንባት በሚያስችል መልኩ ዲያስፖራውን በመደበኛነት ማሳተፍ ሲቻል መሆኑን የኢትዮጵያ ዲያስፖራ አገልግሎት ገለጸ። ለሀገራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ ላበረከቱ 40 የዲያስፖራ አባላት እውቅና እንደሚሰጣቸውም ተገልጿል።

የአገልግሎቱ የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ወንደሰን ግርማ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዳሉት፤ ሀገርን ማሳደግ ከተፈለገ ዲያስፖራውን ወደ መደበኛ ተሳትፎ ማምጣት ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ወንደሰን ገለጻ፤ ዲያስፖራው በቱሪዝምና በኢንቨስትመንት ላይ በመሳተፍና ሌሎችም እንዲሳተፉ በማስተዋወቅ በኩል ሰፊ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ ይህንን እንዲያሳካ መደበኛ በሆነ መልኩ ተሳትፎውን የሚገልጽበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል።

ዲያስፖራው የማይዋዥቅና በሀገር ቤት ወቅታዊ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ተሳትፎን ሊያደርግ ይገባል ያሉት አቶ ወንደሰን፤ ይህ ደግሞ በእኛ ሀገር ብቻ የሚደረግ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮ መሆኑን መረዳት ይገባል ብለዋል።

ዲያስፖራው ከሀገር ቤት ጋር ያለው ግንኙነት ዘላቂ ሀገራዊ ጥቅሞች ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያደርጉ በርካታ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል ያሉት አቶ ወንደሰን፤ የፊታችን ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም የተዘጋጀው የዲያስፖራው የእውቅና መድረክም አንዱ ዓላማ ተሳትፏቸውን ወደ መደበኛ ሁኔታ ማስገባት መሆኑን ጠቁመዋል።

ወቅታዊ ሀገራዊ ጥሪዎችን በማድረግ ፕሮጀክቶችን ለማጠናቀቅ ከዲያስፖራው ሀብት ማሰባሰብ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ላይ መስራት ከዚህ በፊት ሄደንበታል፤ ከዚህ በኋላ የሚኖረን ነገር ተሳትፏቸውን ወደ መደበኛ ደረጃ የማድረስና በሚኖሩበት ሀገርና በኢትዮጵያ መካከል ያለው ግንኙነት እንዲጠናከር ወዳጅነታችን እንዲጎለብት እንዲሰሩ ማስቻል ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ዲያስፖራው በሚኖርበት ሀገር ያሉ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት እንዲያደርጉና እንዲጎበኙ አምባሳደር ሆኖ የመስራት ትልቅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፤ እነዚህን ስራዎች እውን ለማድረግ የሚያግዙ የተለያዩ ስትራቴጂክ ሰነዶች ደግሞ ተዘጋጅተዋል ብለዋል፡፡

አሁን የመጡብንን ጫናዎች ተረባርበን በማሸነፍ አንዱን ምዕራፍ ዘግተናል፤ ከዚህ በኋላ ወደ መደበኛ የዲያስፖራ ተሳትፎ ስራችን መግባት አለብን፤ ሌሎች ሀገራትም ቢሆኑ የተቀየሩት በዚህ መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ዲያስፖራው በቋሚነት ክህሎትና እውቀትን ወደ ሀገር ቤት በማሸጋገር በኢንቨስትመንትና በቱሪዝም ዘርፍ ላይ በስፋት በመሳተፍ፤ ሌሎችም መጥተው በኢንቨስትመንቱ ላይ እንዲሰማሩ በመቀስቀስና የሀገርን ገጽታ በመገንባት በሚኖሩበት ሀገርና በሀገራቸው መካከል እንደ ድልድይ ሆኖ በማገልገል ሚናውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል ።

ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም ለኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ትልቅ ቀን ነው ያሉት አቶ ወንደሰን፤ በሀገራቸው ጉዳይ የነቃ ተሳትፎ ያደረጉ ዲያስፖራዎች እውቅናውን ያገኛሉ፤ በተለይም እውቀት፣ ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ ገጽታ ግንባታ፣ በሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በሀብት አሰባሰብ ላይ የተሳተፉት ተመርጠዋል።

ዝግጅቱ "ኢትዮጵያ ታመሰግናችኋለች ስራችሁ እውቅና ይገባዋል ለማለት ነው"። በሌላ በኩልም እነዚህን አካላት እውቅና መስጠት ማበረታታትና ማነሳሳት ስለሆነ ለምናስበው መደበኛ የዲያስፖራ ተሳትፎ ትልቅ አጋዥ ይሆናል ሲሉም ተናግረዋል።

መደበኛ የዲያስፖራ ተሳትፎን ለመገንባት የምናደርገውን ጉዞ ለማጠናከር የእውቅና ሽልማቱ እንደ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል ነው ሲሉም ተናግረዋል።

# ዴንማርክ የኢትዮጵያ ልማት አጋርነቷን አጠናክራ እንደምትቀጥል አስታወቀች

## - የአዲስ አበባ ከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት መርሐ ግብር ተደንቋል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- ዴንማርክ የኢትዮጵያ የልማት አጋርነቷን አጠናክራ እንደምትቀጥል የዴንማርክ የልማትና ትብብር ሚኒስትር ዳን ጀርገንስ ገለፁ። የአዲስ አበባ ከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት መርሐ ግብር አድናቆት የሚቸረው መሆኑንም ገልፀዋል።

የዴንማርክ የልማትና ትብብር ሚኒስትር ዳን ጀርገንስ ትናንት በአዲስ አበባ ከተማ በጉለሌ ክፍለ ከተማ የከተማ ልማታዊ ሴፍትኔት የሥራ እንቅስቃሴ በጎበኙበት ወቅት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ዴንማርክ እና ኢትዮጵያ የጠነከረ ወዳጅነት ያላቸው መሆናቸውን ጠቁመዋል። በተለይም ሁለቱ ሀገራት በአረንጓዴ ልማት ላይ ያላቸው አቋም በእጅጉ የሚያመሳስላቸው መሆኑን ጠቁመው፤ ሀገራቸውም ለመሰል ፕሮጀክቶች ቀዳሚውን ድጋፍ ታርጋለች ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለምታካሂደው የአረንጓዴ ልማት እና ልማታዊ ሴፍትኔት መርሐ ግብሮች ዴንማርክ ድጋፏን አጠናክራ እንደምትቀጥልም ሚኒስትሩ አረጋግጠዋል። ኢትዮጵያ በዘርፉ የሚያስመሰግንና መሬት ላይ የወረደ ሥራ እየሰራች ነው። በመሆኑም ሁለቱ ሀገራት ካላቸው ወዳጅነት ጭምር ዴንማርክ የሚጠበቅባትን ድጋፍ አጠናክራ ትቀጥላለች፣ ለተግባሩም አድናቆት አላት ብለዋል-ሚኒስትር ዳን ጀርገንስ።

የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ሳሜሬታ ሰዋሰው በበኩላቸው፤ የዴንማርክ መንግስት ከኢትዮጵያ ጋር ባለው ወዳጅነት በበርካታ ጉዳዮች ላይ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። በተለይም በዓለም ባንክ በኩል ዴንማርክ ለልማታዊ ሴፍትኔት የምታደርገው ድጋፍ ትልቅ ቦታ የሚሰጠውና ኢትዮጵያም በዘርፉ የሚለገሳትን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ እያዋለችና ለውጦች እየተመዘገቡ መሆኑን አረጋግጠዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራር ዓባይ በበኩላቸው፤ በአሁኑ ወቅት በከተማ እየተከናወነ ባለው ልማታዊ ሴፍትኔት ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን ገልጸዋል። ይህ ስራ ውጤታማ በመሆኑም አጋር አካላት ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል። በከተማዋ እየተሰሩ የሚገኙ ልማታዊ ሴፍትኔት ሥራዎች በየደረጃው በርካታ ዜጎችን እየጠቀመ መሆኑን አስገንዝበዋል። ከተማ አስተዳደሩ በዚህ ረገድ በሚሰራቸው ሥራዎች ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ በመሆኑ የዴንማርክ መንግስትን ጨምሮ ሌሎች አካላትም ድጋፍ ማድረጋቸውን አስረድተዋል። የከተማ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የአኗኗር ዘይቤ ለመለወጥ በቁርጠኝነት እንደሚሠራም ገልፀዋል።

የከተሞች ልማታዊ ሴፍትኔት እና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ መኮንን ያዒ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በልማታዊ ሴፍትኔት እና ሥራ ፈጠራ መርሐ ግብር ዘርፈ ብዙ ተግባራትን በማከናወን ለበርካታ የአፍሪካ ሀገራት ተምሳሌት የሚሆን ሥራ እየሰራች መሆኑን አስገንዝበዋል። የዓለም ባንክ፣ የዴንማርክ መንግስት እና ሌሎች የልማት አጋሮች ይህን ለውጥ በመመልከታቸው ድጋፍ እያደረጉ መሆኑንም አረጋግጠዋል። በኢትዮጵያ ልማታዊ ሴፍትኔት እና ሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት 450 ሚሊዮን ዶላር በሚሆን በጀት በ11 ከተሞች መተግበሩንና 604ሺ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን አመልክተዋል። ከእዚህም ውስጥ 75 ከመቶ ተጠቃሚዎች የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች መሆናቸውን ገልጸዋል።

# በስድስት ወር 167 ሺህ 850 ዩኒት ደም ሰብስቧል

## ለትግራይ ክልል ከ400 ሺህ ብር በላይ የሚገመት የግብዓት ድጋፍ ተደርጓል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በስድስት ወር ውስጥ 167 ሺህ 850 ዩኒት ደም መሰብሰብ መቻሉን የኢትዮጵያ ደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ፡፡ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ወደ ትግራይ ክልል ከ400 ሺህ ብር በላይ የሚገመት የግብዓት ድጋፍ ተደርጓል፡፡

የኢትዮጵያ የደምና ቲሹ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2015 በመላው ኢትዮጵያ በዓመት 490 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ በስድስት ወር ውስጥ 167 ሺህ 850 ዩኒት ደም ተሰብስቧል።

በስድስት ወር ውስጥ 225 ሺህ ዩኒት ደም እንደሚሰበሰብ ታቅዶ ነበር ይሁንና የደም ለጋሾች ተሳታፊነት በተወሰኑ ወራት ዝቅተኛ በመሆኑ ከዕቅድ በታች አፈጻጸም እንዲመዘገብ ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

ባለፈው የክረምት ወቅት ትምህርት ቤቶች ዝግ በመሆናቸው፤ ወቅቱ ቅዝቃዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ደካማ የደም ልገሳ አፈጻጸም የታየበት መሆኑን አቶ ሀብታሙ አንስተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ከገባ አንስቶ በተለያዩ ዘመቻዎች አማካኝነት የደም ልገሳ እንቅስቃሴዎች መጠናከራቸውን የጠቆሙት አቶ ሀብታሙ፤ ከበዓላት ጋር ተያይዞ የሚከሰተውን የደም እጥረት ለመከላከል ታቅዶ በተደረገው የደም ልገሳ ዘመቻ በአዲስ አበባ ብቻ በአንድ ቀን 960 ዩኒት ደም ተሰብስቧል ብለዋል።

በክልሎች ያለውን የደም ልገሳ አፈጻጸም በተመለከተ የተወሰኑ ክልሎች ላይ ደካማ እንቅስቃሴ መኖሩን የተናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ በአዲስ አበባ፣ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ተናግረዋል።

በአንጻሩ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች ላይ ደግሞ የደም ልገሳ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው። የየክልሎቹ የደም ባንኮች የደም አሰባሰብ ልምዱ እንዲጠናከር የሚረዳ አቅጣጫ ተቀምጦ ከጥቅምት ወር ጀምሮ በስፋት እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በየዓመቱ የደም ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ መምጣቱን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከተጠቃሚዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚያድግ የደም ልገሳ ባህል መኖር እንዳለበትም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፤ የአንድ ሀገር የደም አቅርቦትና ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ተሟልቷል ተብሎ የሚታሰበው በመደበኛነት የደም ለጋሾች ሲኖሩ ነው፡፡ ይህም አጭር የመጠቀሚያ ጊዜ ያለውን ደም



**አቶ ሀብታሙ ታዬ**

በየጊዜው በመለገስና በመተካት የድንገተኛ የነፍስ አድን ሕክምናዎችን ማገዝ ያስችላል።

አሁን ባለው የደም ፍላጎት መሰረት በመደበኛነት በየሦስት ወሩ ደም የሚለግሱ ግለሰቦችን ማግኘት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው ብለዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንዳስታወቁት፤ የደምና ቲሹ ባንክ በዋናነት የደም ማሰባሰብ ስራውን ከበጎ ፈቃድ ደም ለጋሾች ጋር በትብብር በማከናወን የተሰበሰበውን ደም ጥራት የማስጠበቅ ስራ ያከናውናል።

ጥራቱን ጠብቆ እንዲቀመጥ የተደረገውን ደም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎችና አገልግሎቱን ለሚሰጡ ተቋማት በማሰራጨት ኃላፊነቱን እየተወጣ ይገኛል ብለዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ከተደረሰው የሰላም ስምምነት በኋላ በትግራይ ክልል ለሚገኙ ደም ባንኮች 600 ዩኒት ደም እና ከ400 ሺህ ብር በላይ የሚገመት የግብዓት ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ትግራይ ክልል የሚገኙ ደም ባንኮችን መልሶ ለማደራጀት በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ ደም የመሰብሰብ ስራ በተጠናከረ ሁኔታ እስከሚጀምሩ ለታካሚዎች የሚሆን ለአክሱም ደም ባንክ 400 ዩኒት እንዲሁም ለመቀሌ 200 ዩኒት ደም ተሰጥቷል ሲሉ አስታውቀዋል።

በክልሉ የሚገኙ ሶስት የደም ባንኮች በፍጥነት ወደ ስራ እንዲገቡ የተለያዩ ግብዓቶች እየተሟሉላቸው እንደሚገኙም አቶ ሀብታሙ ገልጸው፤ በዚህም ከ400 ሺህ ብር በላይ የሚገመት የዓይነት ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል፡፡

በተደረገው መልሶ የማደራጀት ስራም በአክሱም ከተማ ደም ባንክ ባለሙያዎች ተሟልተው ደም የመሰብሰብ ስራ የተጀመረ ሲሆን በሁሉም ደም ባንኮች ተጠናክሮ እንዲቀጥል እንሰራለን ብለዋል፡፡

# ከፍተኛ አመራሮች ከኅብረተሰቡ ጋር በወለጋ ያደረጉት ውይይት ውጤታማ መሆኑ ተገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ የተመራው የክልሉ ከፍተኛ አመራሮች የተካተቱበት ቡድን በምስራቅ እና በምዕራብ ወለጋ እንዲሁም በቄለም ወለጋ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር ያደረገው ውይይት ውጤታማ መሆኑን የክልሉ ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ፡፡

የቢሮው ኃላፊ አቶ ኃይሉ አዱኛ በትናንትናው ዕለት በዚህ ጉዳይ ላይ ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት፤ በውይይቱ ወቅት በአካባቢዎቹ የሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የመኖር ዋስትናቸው አደጋ ላይ በመውደቁ በአሁኑ ጊዜ ሕዝቡን ከጥቃት ለመታደግ በሸኔ ላይ የተቀናጀ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛል፡፡

ኅብረተሰቡ በወቅቱ በዋናነት የጸጥታ፣ የመሰረተ ልማት፣ የጽንፈኞች በደልና የሥራ አጥነት ጥያቄ ማንሳታቸውን ያወሱት አቶ ሀይሉ፤ ለጥያቄዎቹ ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ሰላም አንኳር ጉዳይ በመሆኑ ጥያቄያቸውን ለመመለስ ኅብረተሰቡ ከመንግስት ጎን በመሆን ጸረ ሰላም ኃይሎችን በቁርጠኝነት እንዲታገል ጠይቀዋል።

የክልሉ መንግስት የክልሉን ሰላምና ልማት አስተማማኝ ለማድረግ ሲሰራ መቆየቱንና አሁንም እየሰራ መሆኑን የተናገሩት የቢሮ ኃላፊው፤ ነገር ግን የሸኔ ሽብር ቡድን አመለካከቱን በጠብመንጃ በሕዝቡ ላይ በኃይል ለመጫን ንፁሀንን መሰረት ያደረገ ጭፍጨፋ እየፈጸመ መሰረተ ልማቶችንም እያወደመ ይገኛል ብለዋል፡፡

አሁንም ቢሆን መንግስት የወደሙ መሰረተ ልማቶች በመጠገን እንዲሁም ግንባታቸው የተቋረጡ ፕሮጀክቶች የማስጀመር ሥራ እንደሚሰራ ቃል መግባቱን አውስተዋል፡፡

ቀደም ሲል የክልሉ መንግስት የሰላም አማራጮችን በማስቀደም በገዳ አባቶችና በአዳ ሲንቄዎች ቡድኑ ወደ ሰላማዊ ትግል እንዲመለስ የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱን ያወሱት አቶ ኃይሉ፤በርካታ ወጣቶች የተደረገላቸውን ጥሪ ተቀብለው ወደ ሰላማዊ ትግል ቢመለሱም ቀሪዎቹ የጥፋት መንገድ መምረጣቸውን አመልክተዋል፡፡

መንግስት የሀገርና የሕዝቡን ሰላም የመጠበቅ ኃላፊነቱን ለመወጣት አሁን ላይ በአሸባሪው ሸኔ ላይ ሁሉንም የጸጥታ አካላት ባሳተፈ መልኩ ሕግ የማስከበር ርምጃ እየወሰደ ነው ያሉት አቶ ኃይሉ፤ ሕዝቡም ወደ መደበኛ ኑሮ ለመመለስ ትብብሩን እያሳየ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ኃይሉ ማብራሪያ፣ ሁሉም ወለጋ ዞኖች በጸጥታ ችግር ለብዙ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋልጠዋል፡፡የኦሮሞና የአማራን ሕዝብ ለማጋጨት ሸኔ እንደሚሰራ ሁሉ ሌሎች ጽንፈኛ ኃይሎች በዞኖቹ በኅብረተሰቡ ላይ በተመሳሳይ መልኩ ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ፡፡ እዚህም እዚያም ያሉ ጸረ ሰላም ኃይሎችን በጋራ አደብ ለማስያዝ የኦሮሚያና የአማራ ክልል አመራሮች የጋራ መግባባት ላይ ደርሰዋል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

# በኦሮሚያ በ6 ወራት 37 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰበሰበ

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ግማሽ ዓመት 37 ቢሊዮን 104 ሚሊዮን ብር ገቢ መሰብሰቡን የኦሮሚያ ክልል ገቢዎች ቢሮ አስታወቀ።

በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የኦሮሚያ ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ መስከረም ደበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በግማሽ ዓመቱ በአጠቃላይ 38 ነጥብ 1 ቢሊዮን ብር በላይ ገቢ ለማግኘት ታቅዶ አፈጻጸሙም 97 ነጥብ 26 በመቶ ሆኗል።

እንደ ወይዘሮ መስከረም ገለጻ፤ የስድስት ወራት ገቢው በመደበኛ መልኩ ከሚሰበሰብ ታክስ እና ከማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ የተገኘ ነው። ከመደበኛ የታክስ ገቢ 31 ቢሊዮን 374 ሚሊዮን ብር በላይ የተገኘ ሲሆን፤ ከማዘጋጃ ቤታዊ ገቢ ደግሞ 5 ቢሊዮን 730 ሚሊዮን ብር ገቢ ተገኝቷል።

የክልሉ አጠቃላይ ገቢ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በ12 ነጥብ 3 ቢሊየን ብር ብልጫ ማሳየቱን የገለጹት ኃላፊዋ፤ በግማሽ ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ የበጀት ዓመቱን ዕቅድ 51 ነጥብ 6 በመቶ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኦሮሚያ ክልል 460 ሺህ ግብር ከፋዮች እንደሚገኙና የግብር ከፋዩ ማኅበረሰብ ግዴታውንና ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚረዱ የተለያዩ ጥረቶች ተከናውነዋል ብለዋል።

በታክስ አሰባሰቡ ሂደት ላይ በግብር ከፋዩ በኩል የደረሰኝ ማጭበርበር ችግር የሚስተዋል መሆኑን አንስተው፤ ችግሩን ለመቀነስ ጥብቅ የሂሳብ ስራና ቁጥጥር ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራቱን አስረድተዋል።

ችግሩ በስፋት በሚታይባቸው ሠራተኞችና ግብር ከፋዮች ላይ ክትትል የማድረግ ስራ በየጊዜው ይከናወናል። የደረሰኝ ቁጥጥር ፣ የታክስ ምዝገባና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ቁጥጥር ማድረግን ጨምሮ ችግሮችን በመለየት የማስተካከያ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል ብለዋል።፡

በቀጣይ ጊዜያት የታክስ አሰባሰቡን ስራ በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግና የአሰራር ሥርዓቱን በጥናት ላይ የተመሰረተ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ ግብር ከፋዮች ታክስን በተመለከተ በወቅቱና በሃቀኝነት እንዲከፍሉ የግንዛቤ ማስጨበጫና የማስተማር ስራዎች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ የተለያዩ መድረኮች ተካሂደዋል።

በሌላ በኩል ግብር ከፋዩን በተቀላጠፈ መልኩ ከማገልገል አኳያ ክፍተቶች አሉ። አገልግሎቶችን ለግብር ከፋዩ ተደራሽ አለማድረግና ማንገላታት በሠራተኞች በኩል የሚስተዋሉ ችግሮች መሆናቸው ተለይቷል ሲሉ ገልጸዋል።

ግብር ከፋዩ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ለሚስተዋሉ ችግሮች 9795 ነፃ የስልክ መስመርን በመጠቀም ቅሬታ ማቅረብ የሚቻል መሆኑን ጠቁመው፤ በግማሽ ዓመቱ በደረሱ ጥቆማዎች መሰረት 45 ችግር የታየባቸውን የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ማስተካከል መቻሉን አስታውቀዋል።

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕዝብ ተወካዮች ምክር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 74 (2) በተሰጣቸው ስልጣን መሰረት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅላቸው ያቀረቧቸውን ተሿሚዎች የውሳኔ ሃሳብ ያቀረቡት አቶ ተስፋዬ ቤልጂጌ ለምክር ቤቱ እንደገለጹት፤ ተሿሚዎቹ ከታችኛው መዋቅር ጀምሮ በተለያዩ እርከኖች በባለሙያነትና በኃላፊነት አገልግለዋል።

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዶክተር አለሙ ስሜ፤ የመጀመሪያ ዲግሪ በልማት አስተዳደር፣ ሁለተኛ ዲግሪ በቢዝነስ አስተዳደርና ሶስተኛ ዲግሪያቸውን ደግሞ በኢንተርፕራይዝ ማኔጅመንት ማግኘታቸውን ጠቁመዋል።

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝም በሲቪል ምሕንድስና የመጀመሪያ ዲግሪ፣ በኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂና ማኔጅመንት ሁለተኛ ዲግሪ እንዳላቸው ተገልጿል።

የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ ደግሞ በደን አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪ፣ ሁለተኛ ዲግሪ በደን ምርት ዘርፍ፣ ሶስተኛ ዲግሪያቸውን በሲቪል ካልቸር ማግኘታቸው ተጠቁሟል።

ሹመቱ የውሳኔ ቁጥር 11/2015 ሆኖ በ10 ተቃውሞ በሁለት ድምጸ ተዐቅቦ በአብላጫ ድምጽ የጸደቀ ሲሆን፤ ተሿሚዎቹም ምክር ቤት ቀርበው ቃለ መሀላ ፈጽመዋል።

ተሿሚዎቹ በውጤታማነትና በቅንነት ሕዝብን ያገለገሉ መሆናቸውንም የምክር ቤቱ አባላት ምስክርነት ሰጥተዋል። ብቃት ያለው የትምህርት ዝግጅት ያላቸው፣ በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ውጤታማ ስራ ያበረከቱ መሆናቸውም ተገልጿል። የተሰጣቸውን የመንግስትና የሕዝብ አደራ የተወጡ መሆናቸውንም ተናግረዋል።

ምክር ቤቱ ከተመለከታቸው አጀንዳዎች መካከል አንዱ የሆነውን የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅን ለማሻሻል የተዘጋጀውን አዋጅ ተመልክቶ ለዝርዝር ዕይታ ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቶታል።

ረቂቅ አዋጁ ወደሀገር በሚገቡ አዲስ ተሽከርካሪዎችና አንዳንድ እቃዎች ላይ የተጣለውን እጅግ በጣም ከፍተኛ የኤክሳይዝ ማስከፈያ ምጣኔ የሚያሻሽል ሃሳብ ይዟል።

አዋጁ በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ ነጻ እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ሰዎች እና ድርጅቶች በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ በመሆናቸው የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ጭምር ከኤክሳይዝ ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ ተፈቅዶ የነበረውን አንቀጽ የሚሰርዝ ሃሳብም አካትቷል።

በተጨማሪም አዋጁ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልበት ማድረግ መንግስት ለሚያከናውናቸው የልማት ስራዎች የሚውል ተጨማሪ ገቢ የሚያስገኝ መሆኑ ስለታመነበት እንዲሻሻል የሚጠይቅ አንቀጽ ይዟል።

በተጨማሪም ለሁለተኛው ምዕራፍ የዘላቂ መሬት አያያዝ የቀረበለትን ረቂቅ አዋጅ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሰራተኞች ደንብን እና የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ሰራተኞች አስተዳደር ደንብን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መርቷል።

በተጨማሪም በኢትዮጵያና በቱርክ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ስምምነትን እንዲሁም የአሳልፎ መስጠት ስምምነት፣ በተመሳሳይም በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት እና በኢትዮጵያ መንግስት መካከል የተደረገውን በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የህግ ትብብር ስምምነትን እንዲሁም የአሳልፎ መስጠት ስምምነትን ለዝርዝር ዕይታ ለቋሚ ኮሚቴ ተመርቷል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እስከዚያው ድረስ ግን ከክልል አስተዳደሮች ጋር በመናበብ እንዲሁም ትምህርት ሚኒስቴርን ባሳተፈ አግባብ የተለያየ ይዘት ያለውን የመምህራን የጥቅማጥቅም ችግር ለመቅረፍ መንግስት አስፈላጊውን ጥረት እንደሚያደርግ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አስታውቀዋል።

በተያያዘ መንግስት በአሁኑ ወቅት ከሁለት ነጥብ አራት ሚሊዮን በላይ ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች እንዳሉት የተናገሩት ዶክተር ዐቢይ፤ የሁሉንም የደመወዝና ጥቅማጥቅም ችግር በአንድ ጊዜ ለመፍታት የሀገሪቷ አቅም እንደማይፈቅድ ይሁንና በሚቻለው ሁሉ የሰራተኛውን ኢኮኖሚ ለማሳደግ ጥረት እንደሚደረግ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ ከዩኒቨርሲቲ አሰራሮች በተለይም ከስራ እርከኖችና ዝውውር ጋር በተያያዙ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለመፍታት ትምህርት ሚኒስቴር በሚያቀርበው ጥናት መሰረት መፍታት ይቻላል።

መምህራን በበኩላቸው የተጣለባቸውን ኃላፊነት በመወጣትና የጠነከረች ሀገር ለመገንባት የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ በሙያቸው የሚያከናውኑትን ስራ ማሳደግ እንዳለባቸው አንስተዋል። ከዚህ አንጻር የሚያቀራርቡ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ከፋፋይ ሃሳቦችን ከአዕምሯቸው ማስወገድ እንዳለባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አሳስበዋል።

ምሁራን ለሀገራቸው ያላቸውን አበርክቶ ለማሳደግ ከሰፈር ፖለቲካ ወጥተው አገራዊ ዕይታቸውን ሊያሰፉ ይገባል ሲሉ ዶክተር ዐቢይ ተናግረዋል። የሰፈር ፖለቲካ ሀገር ከማፍረስ የዘለለ ጥቅም የለውም። የሰፈር አጀንዳ ሀገር ለማፍረስና የባዕዳንን ተልዕኮ ለማስፈጸም ካልሆነ እንደሀገር አይጠቅመንም። ያለችንን ሀገር በጋራ ለመገንባት ሀገራዊ እሳቤና አንድነት ያስፈልጋል ብለዋል።

እኔ የምፈልገው ብቻ ይሁን ከሚል እሳቤ በመውጣት ጎረቤቴ፣ ጓደኞቼ፣ ቤተሰቦቼና ሌላው ብሔር ምን አለው የሚለውን መያዝ ይገባል። ያኔ የእኛ የምንለውን አንዳንዴ እየተውን በመቻቻል መኖር እንችላለን ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

እንቁላል ከእጅ ካመለጠ ወደነበረበት እንደማይመለስ ሁሉ ሀገርም ከፈረሰች በኋላ ወደ አንድነቷ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው። ይህን የተረዳ ምሁራዊ አስተሳሰብ ሊኖረብን ይገባል ሲሉ ተናግረዋል። ምሁራን ለትውልድ በተለይም ለልጆቻችን የተሻለች ሀገር ለመገንባት ከጽንፈኝነት ነጻ የሆነ አስተሳሰብን ማራመድ ይገባል።

ከዚህ ባለፈ ዩኒቨርሲቲዎች የሴቶችን ተሳትፎ በማሳደግ፣ የምርምር ስራዎችን በማዳበር፣ የአካል ጉዳተኞችን ሚና በማሳደግና በአካታችነት የጀመሯቸው ስራዎች ላይ ትኩረት ሊያደርጉ እንደሚገባ ዶክተር ዐቢይ አሳስበው፤ ጉዳት የደረሰባቸውን ዩኒቨርሲቲዎች በመደገፍ ረገድ የተቻለው ሁሉ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

የምሁራኑ ውይይት በቀጣይ በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ እንደሚከናወንና የማጠቃለያ ውይይቱ ደግሞ በተመረጠ አንድ ዩኒቨርሲቲው ውስጥ እንደሚከናወን ተገልጿል።

# በብሔራዊ ደህንነት ላይ ያተኮረ የፓናል...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ኮሌጁ በስትራቴጂካዊ የደህንነት ጉዳዮች መካከለኛ አመራሩን በማሰልጠን ወደ ከፍተኛ አመራር በማሳደግ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር እያካሄደ ነው።

ተለዋዋጭ በሆነው የዓለም አቀፍ እና የቀጣናዊ የደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ አዳዲስ ዕውቀቶችን ማግኘት ተገቢ በመሆኑ እና የተለያዩ የዕይታ ደረጃዎች በመኖራቸው አምባሳደሮች፣ ጥናት አድራጊዎች፣ የደህንነት ሴክተሩ የተለያዩ ዕይታዎች ወደ አንድ ማምጣት ኮሌጁ ለሚሰጣቸው የጥናትና ምርምር ስራዎች ጠቀሜታው የጎላ ነው ብለዋል።

በኮሌጁ አዘጋጅነት ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገው መድረክ በተለይ በቀጣናው የውሃ ጂኦፖለቲካዊ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴዎች እና የዩክሬንና ሩሲያ ጦርነት በሚያሳድሯቸው የደህንነት ችግሮች ወቅታዊ ተሞክሮና ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ መሆኑንም አክለው ተናግረዋል።

ውይይቱ ከሀገራዊ፣ ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ወቅታዊ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታዎች ጋር ተያያዥነት ያለውና ወደ ፊት ሊከሰቱ የሚችሉ የደህንነት ችግሮች ላይ የጋራ ግንዛቤ ከመፍጠር ባሻገር ኮሌጁ የረጅም ጊዜ ልምድ ካላቸው አንጋፋ አምባሳደሮች ተሞክሮና የዕውቀት ሽግግር የሚወስድበት ነው ብለዋል።

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ መከላከያ ዋር ኮሌጅ የጦርነት ንድፈ ሃሳብና ስትራቴጂ ጥናት ትምህርት ክፍል ኃላፊ ኮሎኔል ቶማስ ዓለሙ፣ በወቅታዊ የዓለም ጉዳይ በሩሲያ እና በዩክሬን መካከል የሚደረገው ጦርነት ያደጉና ያላደጉ አገራት ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን አስታውሰው፤ በሀገራችንም ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ፣ ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ የደህንነት ሁኔታዎች ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። በመሆኑም በቀጣይ ይሄንን ለመቋቋም ኢትዮጵያ እና የቀጣናው ሀገሮች ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው የሚጠቁም ነው ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ ጎረቤት ሀገራት ሶማሊያ ለረጅም ጊዜ ችግር ውስጥ የምትገኝ በመሆኑ ችግሩ በቀጣናው ሀገሮች በተለይም በኢትዮጵያ፣ በኬንያ፣ በጂቡቲ ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው። የዚህ ተፅእኖ ምንጭ ደግሞ ዓለምአቀፍ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ አካል የሆነው የአልሸባብ እንቅስቃሴ በብሔራዊ ደህንነት ላይ ያለው የስጋት ደረጃ ለመለየትና ችግሩን ለመቋቋም መከተል ስለሚገባው ስትራቴጂ የተመላከተ መሆኑንም አስረድተዋል።

የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት በጋራ የሚያስተዳድሩት የምስራቅ አፍሪካ ተጠባባቂ ብርጌድ በመጠቀምም በወታደራዊ፣ በዲፕሎማሲ እና በሌሎች ጉዳዮች በመተባበር ሊሰራ የሚቻልባቸው እድሎች ያሉ ሲሆን፤ በየሀገራቱ መካከል በሚኖረው ግንኙነትም የሁለትዮሽ ግንኙነቶች ኃይልን በማስተባበር ሽብርተኝነትን መቋቋም የሚቻልባቸው እድሎች እንዳሉ ጠቁመዋል።

ከውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት ጥናት ያቀረቡት ዶክተር ውብእግዜር ፈረደ በበኩላቸው፤ ቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ጂኦፖለቲካዊ ጉዳዮች ባለፉት 100 ዓመታት ሀገራችንን ሲጎዱ የመጡ መሆኑን አንስተዋል።

ከህዳሴ ግድቡ መጠናቀቅ በኋላ ኢትዮጵያ የቀጣናውን ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታዎች የመምራት እድሎች እንዳሏትም ጠቅሰው፤ በሃሳብ የበላይነት ላይ የሚደረገው ግንባር ተቀናጅቶ መሄድ አለበት ብለዋል።

በኢትዮጵያ በኩል በቀጣናዊ ጂኦፖለቲካዊ ሁኔታዎች ላይ ወቅታዊ ግንዛቤ በማዳበርና አዳዲስ አጀንዳዎች በመቅረፅ የቀይባህር ፖለቲካ እንዲሁም አድዋን በመጠቀም የጥቁር ብሔርተኝነት ላይ ሥራ ልትሰራ እንደሚገባ አመላክተዋል።

በፓናል ውይይቱ ከውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት፤ ከፍሬድሪክ ኤበርት ስቲፍቱንግ፤ ከምክክር ጥናትና ትብብር ማዕከል የመጡ አንጋፋ ዲፕሎማትና አምባሳደሮች ተሳትፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የተፋሰስ ልማቱን የማጠናከሪያ ወቅት!

እየተጋመሰ ያለው ጥር ወር ለኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ብዙ ፋይዳ አለው፡፡ ወሩ የመኸር አዝመራ የመሰብሰቡ ስራ የሚጠናቀቅበት፣ አርሶ አደሩ አንጻራዊ እፎይታ የሚያገኝበት ወቅት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አርሶ አደሩ ይህን ወቅት ሌላ ልማትም እያዋለው ይገኛል፡፡ ይህን ወቅት በአፈር መሸርሸር ሳቢያ ለምነቱ እየተሟጠጠ ያለውን መሬቱን በተፋሰስ ልማት የሚያክምበት ማድረግ ከጀመረ በርካታ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡

በሀገሪቱ በዚህ ወር የተፋሰስ ልማት ስራ በከፍተኛ ደረጃ ይከናወናል፡፡ መንግስት በዚህ ላይ ዝግጅት አድርጎ ነው ስራው እንዲፈጸም የሚያደርገው፡፡ ዘንድሮም እንዳለፉት ዓመታት መንግስት ለዚህ የተፋሰስ ስራ ከፍተኛ ዝግጅት አድርጓል፡፡

ግብርና ሚኒስቴር ከጥር ወር 2015ዓ.ም ጀምሮ ለሚከናወነው የተፋሰስ ልማት ሥራ አስፈላጊው ዝግጅት ማድረጉን አስቀድሞ አስታውቋል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የተፋሰስ ልማት ስራው እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ከመገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች መረዳት እንደሚቻለውም አርሶ አደሩ በዓመታዊው የተፈጥሮ ሀብት ልማት ስራው ላይ ተጠምዷል፡፡

ሚኒስቴሩ አምስት ሺህ የማኅበረሰብ ተፋሰሶችን ለማልማት የአምስት ዓመት ፕሮጀክት ቀርጾ ከሁለት ዓመት በፊት ወደ ትግበራ መግባቱን አስታውሶ፣ የዚህ ወቅት ሥራም ፊዚካል የሚባለው ወይም በውጫዊው የልማት ሥራ ላይ ያተኮረ መሆኑን አመልክቷል፡፡ እንደ ሀገር ለተያዘው ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ጥረትም በጉዳት ከልማት ውጭ የሆነ መሬት በአፈር ጥበቃ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመሬት አቅርቦት የማሻሻል ሥራ ባለፉት ሶስት ዓመታት ሲሰራ መቆየቱንም ነው ያመለከተው፡፡

በሀገሪቱ ለበርካታ ዓመታት በተካሄደው የተፋሰስ ልማት ስራ አፈርን በጎርፍ ከመሸርሸር መታደግ የሚያስችሉ ተግባሮች ተከናውነዋል፡፡ እርከን በመስራት፣ ጋቢዮን በመገንባት፣ እነዚህ ስራዎች በተከናወኑባቸው አካባቢዎች የዛፍና የመሳሰሉትን ችግኞች በመትከል በተከናወነው የተፋሰስ ልማት በክረምት ወቅት በጎርፍ የሚታጠበውን ለም አፈር ለመቀነስ እየተቻለ ይገኛል፡፡

የአባይ ግድብን ሊደርስበት ከሚችለው የደለል አደጋ መታደጊያው አንዱ መንገድ ይሄው የተፋሰስ ልማት ስራ መሆኑ ግንዛቤ ተይዞበት ለዓመታት የተፋሰስ ልማት ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው፡፡ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻውንም ከተፋሰስ ልማት ጋር በማስተሳሰር በበጋ ወቅት የተሰሩትን እርከንና የመሳሰሉትን የአፈር ጥበቃ ስራዎች በክረምቱ የዛፍና የተለያዩ እጽዋት ችግኞችን በመትከል በአካባቢዎች ላይ ለውጥ ለማምጣት ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡

የተፋሰስ ልማትን ማካሄድ ለኢትዮጵያ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ሀገሪቱ አሁን ብቻ አይደለም በመጪዎቹ ጥቂት የማይባሉ አመታትም ኢኮኖሚዋ ከግብርና ስራዋ ጋር በእጅጉ ቁርኝት እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ ግብርናው የምግብ ዋስትናን ማረጋገጡን፣ የሀገሪቱ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ በመሆን ማገልገሉን ይቀጥላል፡፡ ግብርናው መዋቅራዊ ለውጥ እስከሚያመጣ ድረስ ብዙ ሊሰራበት የግድ ነው፡፡

ለዚህም ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ከሚደረግ ርብርብ በተጨማሪ ለምርትና ምርታማነት ወሳኙ የሆነውን አፈር መጠበቅ የግድ ይሆናል፡፡ ለእዚህ የአፈር ጥበቃ ስራ ደግሞ የተፈሰስ ልማት ወሳኙ መሳሪያ ነው፡፡ የተፋሰስ ልማቱ የአፈር መሸርሸርን ብቻ ሳይሆን ለማስቀረት የሚረዳው፣ የዓለማችን ችግር እየሆነ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል፣ የዓባይ ግድብን ከደለል ለመታደግ እና የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብሩን ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግም ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ሁሉ አኳያም የተፋሰስ ልማቱ ላይ ርብርብ ማድረግ የግድ ሆኖ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ሀገሪቱ በተፋሰስ ልማት ዓመታትን የዘለቀች እንደመሆኗ በልማቱ በኩል አርሶ አደሩን ጨምሮ ሌሎች ባለድርሻ አካላት በልማቱ ላይ በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል፤ አርሶ አደሩ በተፋሰስ ልማቱ ያካበተው እውቀት እንዳለም ይታሰባል፡፡ በመንግስት በኩል ቁርጠኝነቱ አለ፡፡ ይህን ሁሉ አቀናጅቶ ልማቱን ከአሁኑም በላይ አጠናክሮ ማከናወን የዚህ ወቅት ስራ መሆን ይኖርበታል፡፡

እንደሚታወቀው የተፋሰስ ልማቱ በሁለት መንገድ ነው ሲከናወን የቆየው፡፡ አንዱ በሴፍትኔት መርሀ ግብር ሲሆን ሌላው ደግሞ በማኅበረሰብ ደረጃ በዘመቻ የሚካሄደው ነው፡፡ በሴፍቲኔት መርሀ ግብር የሚካሄደው የተፋሰስ ልማት በጀትና ሰራተኞች ተመደበውለት የሚፈጸም ነው፡፡ ሌላውና በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው የተፋሰስ ልማት ደግሞ በማኅበረሰብ ደረጃ በዘመቻ የሚካሄደው የተፋሰስ ልማት ስራ ነው፡፡

ይህ በማኅበረሰቡ ደረጃ የሚካሄደው የተፋሰስ ልማት የጥር ወርን ይዞ የሚካሄድ እንደመሆኑ ወቅቱን በሚገባ መጠቀም ይገባል፡፡ አርሶ አደሩ በአሁኑ ወቅት ያለውን በቂ ጊዜ በመጠቀም፣ ግብርና ሚኒስቴር የሚያደርገውን ድጋፍና ክትትል በማጠናከር የተፋሰስ ልማቱ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ኢትዮጵያ ብዙ መልማት የምትፈልግ ሀገር ናት፣ በአሁኑ ወቅት በእጇ ያለው ዋና የልማት መሳሪያዋ ግብርናዋ ነው፡፡ ግብርናዋ ደግሞ በእርሻ ስራ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ከዚህ ግብርና ምርትና ምርታማነትን መጠበቅ የሚቻለው ለተፋሰስ ልማትም ትኩረት በመስጠት ነው፡፡ በደን መመናመን ሳቢያ የሀገሪቱ ለም አፈር በከፍተኛ ሁኔታ እየተሸረሸረ ይገኛል፡፡ ይህን አፈር መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

ለዚህ ደግሞ የተፋሰስ ልማት ወሳኝ ስለመሆኑ ልማቱን በማካሄድ የታዩ ለውጦች አመላክተዋል፤ የተፋሰስ ልማት ስራዎችን ተከትሎ አፈርን ከመሸርሸር መታደግ እንደሚቻል ግንዛቤ ከመጨበጥም በላይ ማድረግ እንደሚቻል ታይቷል። በአንዳንድ አካባቢዎች ደርቀው የነበሩ ምንጮች ውሃ ወደ ማፍለቅ የተመለሱበት፤ የተተከሉ ችግኞች ዛፍ በመሆን መሬቱን እየታደጉባቸው ሁኔታዎች ስለመኖራቸው መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከአካባቢው ሸሽተው የነበሩ አእዋፋት እና የዱር እንስሳት የተመለሱበት ሁኔታ እንዳለም እየተገለጸ ነው፡፡

ይህ ሁሉ የተፈሰስ ልማቱን አጠናክሮ የመቀጠልን ፋይዳ በሚገባ ያመለክታል፡፡ አርሶ አደሩ ለበርካታ አመታት ልማቱን ያካሄደ እንደ መሆኑ ብዙ ተሞክሮዎችን አግኝቷል፡፡ በዚህ ላይ የግብርና ሚኒስቴር የዘርፉ ባለሙያዎች ምክርና ድጋፍ አብሮት አለ፡፡ ይህን አቅም በሚገባ በመጠቀም የተፋሰስ ልማቱን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# "የትውልዴ እብደትና የውጤቱ ፀፀት"

(በጌታቸው በለጠ/ዳግላስ ጴጥሮስ)

### የቅድመ ሙግት መደላድል፤

የጽሑፌ ርዕስ የተዋቀረባቸውን ቃላት ለመበየን በእጅጉ አስቸጋሪ እንደሚሆን ይገባኛል። አራቱ ቃላትና በመካከላቸው የተደነቀረችው "ዬ" የተሸከመችውን "የእኔ" የሚለውን ባለቤት አመላካች ምዕላድ በአግባቡ ተንትኖ ለአንባቢያን የልቡን ለማድረስ "ከልብ የሆነ" ዝርዝር ንባብና ጥናት ይጠይቃል። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ጊዜ መፍጀቱ የማይቀር ነው።

ቢሆንም ግን አንኳሩ ሃሳብ እንደሚፈለገው ባይብራራም የጉዳዩ አሳሳቢነት ግድ ስለሚለንና በጋራ ውይይት ተላምጦ ሊደቅ እንደሚችል በማመን ርዕሰ ጉዳዩን ለመነካካት ግድ ብሎናል። ይህ ከተራራ የገዘፈ አሚጋች ርዕሰ ጉዳይ በአንድ ውይይት ለተግባቦት ይደርሳል የሚል እምነት ባይኖረንም ከዛሬ ጀምሮ ብናብላላው ክፋት ስለሌለው እነሆ ለጋዜጣው ቤተሰቦች የመንደርደሪያ ሃሳቡን እንደሚከተለው ይድረስ እንላለን።

ሞጋቹ ጥያቄ የሚጀምረው "አንድ ትውልድ የሚሸፍነው የጊዜ ርዝመት ስንት ዓመት ነው?" ከሚለው ይሆናል። እውነቱን ለመናገር ይህ አወዛጋቢ ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ ሲጠየቅ ዓመታት ቢነጉዱም እስከ ዛሬ ድረስ ይህ ነው በሚባል ስምምነት ላይ የተደረሰ አይመስልም። ስለዚህም መልሱ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም ማለት ነው።

"እብደትስ ምንድን ነው?" ይህም ቃል ቢሆን መዛግብተ ቃላት ከደነገጉለት ፍቺ ላቅ ያለ ሥነ ልቦናዊና ማሕበራዊ ጽንሰ ሃሳብ እንደተሸከመ እንረዳለን። ስያሜው በሐኪሞች የማይወደድ እንደሆነም አይጠፋኝም። የባለሙያዎቹ ምርጫ "የአእምሮ ሕመምተኛ" ወደሚለው እንደሚያጋድልም ይገባኛል። ለማንኛውም ብዙኃኑ በሚስማሙበት የተለምዶ አገላለጽ ተጠቅመን በሃሳቡ ላይ ጥቂት እንቆዝም።

በማንኛውም ግለሰብ ሕይወት ውስጥ የመጠን ልዩነት ይኖር ካልሆነ በስተቀር እያንዳንዱ ሰው በማያመልጠው ጊዜያዊ አለያም ዘላቂ ወፈፍታ እንደሚለከፍ የሥነ ልቦና በሳሎች በጥናታቸው አረጋግጠናል ብለውናል። በአጭሩ እብደት በሁኔታዎች፣ በጊዜና በቦታ የሚወሰን የአስተሳሰብና የድርጊት ወለፈንዴነትና ግራ አጋቢነትን የሚወክል ጽንሰ ሃሳቡ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል።

"የእኔ ያልከው ትውልድ የሚወክለው ዘመንስ የትኛውን ነው?" ለዚህም ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ ለመስጠት ብዕሬ መንተባተቡ አይቀርም። ይህም ተባለ ያ ችግሩ ጊዜ የሚሰጥ ስላልሆነና አደጋውም በቀላሉ መታየት ስለማይገባው የውጥር በተያዝንባቸው ዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮቻችን ዙሪያ ልብ ተቀልብ ሆነን ልንመክርበት ወቅቱ ራሱ የሚሞግተን ይመስለኛል።

ይህ ጸሐፊ በውጭ ሀገር ትምህርት ላይ በነበረበት አንድ ዕለት "የአንድ ትውልድ የዘመን ስሌት ስንት ይሆናል?" የሚል ክርክር በተማሪዎች መካከል ተነስቶ እኛ ተማሪዎችም ሆንን ፕሮፌሰራችን በተቀራራቢ ሃሳብ ላይ ለመድረስ ተስኖን "ሲተኙ ነገር ያገኙ" እንዲል የሀገሬ ብሂል፤ ሙግቱ በይደር ይተላለፍ ተብሎ መወሰኑን አስታውሳለሁ።

በዚህ የጋራ ስምምነት ላይ በአሜንታ ተስማምተን ለሻይ እረፍት እንደወጣን ነገሩ እጅግ ስለከነከነኝ ወደ ፕሮፌሰራችን ጠጋ ብዬ ""የእርስዎን ግምታዊ ምልከታ ሊነግሩኝ ይችላሉ?" ብዬ በትህትና ስጠይቃቸው፤ ራሳቸውን ወዲያ ወዲህ እያወዛወዙና በርካታ ታሪካዊና ማሕበራዊ ጉዳዮችን እያጣቀሱ "ምናልባትም ከሃያ አምስት እስከ ሠላሳ አምስት ዓመት ሊሆን ይችላል" የሚል ፍንጭ ሰጥተውኝ ነበር። በግሌ የመምህሬ ጥቆማ ለዚህ ጽሑፍ የመነሻ ሃሳብ ግብዓት ቢሆን የሚበጅ ስለመሰለኝ ካለፈው ሦስት አሥርት ዓመታት ጀምሮ እየኖርንበት ያለውን ይህንን ወቅት እንደ አንድ የትውልድ ዘመን በመውሰድ ቅኝቴን ገድቤበታለሁ።

"ፀፀት" - ባላደረግሁት ወይንም ባደርገው ኖሮ፣ ባይሆን ወይንም ባይፈጸም ኖሮ፣ ባልተናገርኩ ወይንም በተናገርኩ ኖሮ ወዘተ. የሚያሰኘውን የውስጥ ሙግትና ሙብከንከንን ይወክላል። ሙብከንከኑ ቁጭትም ያዘለ መሆኑን ልብ ይሏል። ስሜትን ወጥሮ እንደ ሻህላ (ሻጋታ) ውስጥን የሚያመነዥከው ይህ አሉታዊ እህህታ ለቅጽበት ብቅ ብሎ የሚጠፋ ወይንም ለረጂም ጊዜ ሊሰነበት የሚችል አቅም ያለው መሆኑንም ማስታወሱ አይከፋም። የመደላድሉ ጥቁምታ እስከዚህ ድረስ ካጓጓዘን ዘንዳ ወደ ዋናው የመድረሻችን ማጠቃለያ ለመድረስ እንድንችል የንባብ ወጋችንን እንግፋበት።

### የዘመናቸውን ትውልድ እብደት የሞገቱ ቀደምት ጸሐፍት፤

"ኦሮማይ" - በሚል ርዕስ እጅግ ተነባቢ የሆነ የመጽሐፍ ገጸ በረከት አበርክቶልን እንደ ተወርዋሪ ኮከብ ከስሞ የጠፋብን ነፍሰ ኄሩ ደራሲያችን በዓሉ ግርማ የራሱን ዘመንና ትውልድ የሄሰው እንዲህ በማለት ነበር። "ሩጫ ላይ ያለች ሀገር ናት። ቢከፋም ቢለማም ድርጊት! አዲሱ ትውልድ የድርጊት ትውልድ ነው። ጊዜ ያጥረናል፣ ጊዜ የለንም፣ ችኩል ትውልድ ነን። ያበደ ትውልድ። እውነት እብዶች ነን! ያሮጌው ትውልድ ሙጣጭ፤ ያዲሱ ትውልድ የበኩር ልጅ። ያንዱ መጨረሻ፤ የሌላው መጀመሪያ መሆን እብደት ነው። ያሮጣል...ንግግር! ንግግር! ንግግር! የጊዜያችን ምልክት ነው። ብዙ ንግግር ትንሽ ሥራ። የለም! ሌሎች ደግሞ ከስብሰባ ጋር ያያይዙታል። ስብሰባ! ስብሰባ! ግምገማ! ግምገማ! ብዙ ስብሰባ፣ ብዙ ግምገማ ትንሽ ውጤት" (ገጽ 13 እና 48)።

ይህ መጽሐፍ ከተጻፈ ከአርባ አመት በኋላ ያለው ይህ "የእኔ" ትውልድስ ከዘመነ በዓሉ ግርማ ትውልድ የሚለየው በምንድን ነው? የወፈፍታው ባህርይስ እንዴትና በምን ሊበየን ይችላል? በግሌ ልዩነት ያለው አይመስለኝም። "ቀልቀሎ ስልቻ፤ ስልቻ ቀልቀሎ" እንዲሉ ወይንም "ትሻልን ሰድጄ ትብስን አገባሁ" እያለ ግፍግፍ እንዳለው የጥንቱ አባወራ በግሌ ይህ ነው የሚባል መሻሻል አይታየኝም። እዚህ ድምዳሜ ላይ የደረስኩት "ጨለምተኛ" ሆኜ ሳይሆን እውነቱ ያፈጠጠ ስለመሰለኝ ነው።

እንደ በዓሉ ግርማ ሁሉ እሸቱ ብሩ ይትባረክ የተባሉ የማሕበራዊ ሚዲያ ሞጋችም ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ዘመኑንና ትውልዱን በተመለከተ የጥያቄ ውሽንፍር አዥጎድጉደው የልባቸው አልደርስ ቢላቸው "እኔን ታከተኝ የቀረውን እናንተ አክሉበት" በማለት ሃሳባቸውን በእንጥልጥል የደመደሙበትን ጽሑፍ እንደሚከተለው እጠቅሳለሁ።

ወደ 8ኛ ገጽ ዞሯል

# ተጠየቅ

# ‹‹ኢ-መደበኛ ነጋዴዎችን ህጋዊ የማድረግ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው››

*- አቶ ሙሉጌታ ተፈራ*
*የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ*

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በከተማ አስተዳደሩ የተጣለበትን የገቢ መሠብሰብ ኃላፊነት በሚገባ ለመወጣት እና ከተማዋ ከምታመነጨው ኢኮኖሚ በበጀት ዓመቱ የ70 ቢሊየን ብር ዕቅድን ለማሳካት ከፍተኛ ጥረት ሲያደርግ መቆየቱን ይገልጻል። በስድስት ወራት ውስጥም ዘርፈ ብዙ ስራዎችንና ቅንጅታዊ አሰራሮችን በማከናወን እያደገ የመጣውን የግብር ከፋይ ቁጥር ተደራሽ ባደረገ መልኩ ቀልጣፋና ውጤታማ ስራ ማከናወኑን አስታውቋል፡፡ ስመሆኑ ተቋሙ ከተጣለበት መንግስታዊ ኃላፊነት አንጻር ህገወጥ ነጋዴዎችን ወደ ህጋዊ መስመር አምጥቷል፣ ህገወጥ አሰራሮችን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ያሉ ብልሹ አሰራሮችን በማረምና በማስተካከል ረገድ ምን ያህል ተጉዟል። ከግብር ስወራና ከመሳሰሉት ጋር የተያያዙ ስራዎች በሚፈለገው ልክ የክትትልና የቁጥጥር ስራው ተሰርቷል። በእነዚህና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ አቶ ሙሉጌታ ተፈራ ምላሽ ሰጥተዋል።**

**አዲስ ዘመን፡- በበጀት ዓመቱ ግብር ስመሰብሰብ ስትነሱ በቀዳሚነት የተቀመጡ መርሆች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** የከተማችንን መሰረታዊ ፍላጎቶችና ጥያቄዎችን ለመመለስ በመጀመሪያ ትኩረት የሚሰጠው ገቢ ማግኘት ላይ ነው።ይህ ቢሮ ደግሞ የከተማ አስተዳደሩ የሚፈልገውን ገቢ በመሰብሰብ ረገድ ቀዳሚው ሚና እና ተግባሩን እንዲወጣ ኃላፊነት የተጣለበት ተቋም ነው። በመሆኑም ይህን ገቢ ለመሰብሰብና የከተማዋ ዕድገት ለማምጣት በግልጽ የተቀመጠ ነው።በመርህ ደረጃም መግባባት የተደረሰበት ከመሆኑም በላይ ኃላፊነቶችም በግልጽ የተቀመጡ ናቸው።

የገቢው አሰባሰቡ ዘመናዊነት የተከተለ እንዲሆን፣ ቀልጣፋ አሰራር እንዲተገበር፣ ግብር አሰባሰቡ ፍትሃዊ እንዲሆን፣ በተጨማሪም ተደራሽ በሆነ መንገድ መስራት የሚለውም ቀዳሚው ሥራችን ነው።

እንደ ከተማ አስተዳደሩ ይህ ቢሮ ከፍተኛው ገቢ መሰብሰብ እንዳለበት ይታመናል።ከተማ አስተዳደሩ በበጀት ዓመቱ የ100 ቢሊዮን ብር በጀት አውጇል።ይህ በጣም ከፍተኛ የገንዘብ መጠን ነው።ይሁንና ከዚህ ውስጥ የከተማዋ ከፍተኛ ገቢ የሚሸፈነው ወይንም 70 ቢሊዮን ብር በገቢዎች ቢሮ በሚሰበሰበው ነው፡፡

ቢሯችን ከሚሰበስበው 70 ቢሊዮን ብር በተጨማሪ ቀሪው ደግሞ ከተለያዩ ተቋማት በሚሰጡት አገልግሎት እና የተለያዩ አግባቦች የሚሰብሰብ መሆኑ ይታወቃል።ስለዚህ ትልቅ ሥራ እንደሚጠበቅብን አውቀንና ተማምነን ነው ወደ ሥራ የገባነው።ከአመራር እስከ ባለሙያው ምን መሠራት አለበት የሚለው የሥራ ድርሻም በሚገባ ኃላፊነት ወስደን ነው ወደ ተግባር እንቅስቃሴ የገባነው።

በመሆኑም እንደተቋም በ2015 በጀት ዓመት 70 ቢሊዮን ለመሰብሰብ በተጀመረው ሥራ በርካታ ተግባራትን አከናውነናል።ሥራችንን ስንጀምር ሰፊ የንቅናቄ መድረኮችን በተለያየ ቦታዎች አካሂደናል።በዚህም በጀመርነው ንቅናቄ በየቅርንጫፎቻችን ምን መሠራት አለበት በሚለው ታቅዶ አስፈላጊ ተግባራት ተከናውነዋል።በከተማ አስተዳደሩ በሚገኙ ሁሉም ወረዳዎች ከሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎችና አመራሮች ጋር የተግባቦት ሥራዎችን በሰፊው በማከናወን ለእቅዳችን እና ግባችን መሳካት መሰረት ተጥሏል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ እነዚህን ተግባራት ለማከናወን ከማን ጋር ምን መሥራት አለበት በሚለውም ላይ ነው ትኩረት የሰጠው።በዝግጅት ምዕራፍ ጀምሮ በጣም ትልቅ ሥራዎች የተከናወኑበት ነው።ይህን በማድረጋችን ባለድርሻ አካላትን እንደየአስፈላጊነቱ ለማሳተፍ እና እቅዳችንን ለማሳካት ተገቢውን እርምጃ ሄደናል ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ከተማዋ አለኝ የምትለው ሁነኛ የግብር ከፋይ ስንት ነው?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** በከተማችን የግብር ከፋዮች ቁጥር በየጊዜው እየጨመረ ነው።በተለይም በምንፈጥራቸው መድረኮችና የተግባቦት ሥራ በርካቶችን ወደ ህጋዊ መስመር በማስገባት ገቢ መክፈል እንዳለባቸው አምነው እየከፈሉ ነው።ከ449 ሺህ ግብር ከፋዮች ውስጥ 93 ከመቶ የሚሆኑት በግብር ማሳወቅያ ወቅት ወደ ቢሯችን መጥተው ኃላፊነታቸው ተወጥተዋል።ይህ ሊሆን የቻለው በየጊዜው በምናከናውናቸው ተግባራት ነው።ከዚህ ውጭ ያሉትን ቀሪዎቹ ደግሞ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ተገቢው የማሳወቅ ስራ በመስራት ገቢ እንዲሰበሰብ ተደርጓል።



> ## በ
> መርካቶ አካባቢ የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ በዚህ ገበያ ሰፋ ያለ ነገር አለ። በህገ ወጥ መንገድ ሲሰሩ የነበሩትን ወደ ህጋዊ መንገድ እንዲመጡና ህጋዊ የሆኑ አካላት ደግሞ እንዲበረታቱ በስፋት ሰርተናል፡፡ በዚህም 35 ሺህ የሚደርሱ ግብር ከፋዮች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው እንዲሰሩ አድርገናል

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በስድስት ወራት ምን ያክል ገቢ ሰብስቧል?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** ከላይ እንደተገለጸው በበጀት ዓመቱ በሰፊው መስራት አለብን ብለን ነው የተነሳነው።በእቅዳችን ከተያዘው 60 ከመቶ መሰብሰብ ችለናል።ቀሪው 40 ከመቶ ደግሞ በቀሪው ጊዜ ይሰበሰባል።ይህን ለማድረግም ከመጀመሪያው ጀምሮ በከተማ ከንቲባ ጭምር ትልቅ የንቅናቄ ሥራዎች ሰርተናል።ይህን ለማሳካትም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋርም በተቀናጀ አሰራር ዘርግተናል።ብልሹ አሰራርንም ለማቃለል ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ነው እየሰራን ያለነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የቢሮው የ2015 የበጀት ዓመት ዕቅድ ከ2013 እና ከ2014 ዓ.ም ንፅፅር ምን ይመስል?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** በአጠቃላይ ቢሮው ከዓመት ወደ ዓመት አሰራሩን በማዘመን፣ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም፣ በአመራሩና በፈፃሚው መካከል ከፍተኛ መናበብና ተነሳሽነት በመፍጠር የገቢ አሰባሰብ አቅሙን እያሳደገ ሲሆን ይህም በ2013 በጀት ዓመት 42.40 ቢሊዮን ብር የሰበሰበ ሲሆን በ2014 በጀት ዓመት ደግሞ 55.77 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ችሏል። በ2015 በጀት ዓመት ቢሮው 70 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ያቀደ ሲሆን ባለፉት ስድስት ወራት ቢሮው ለመሰብሰብ በዕቅድ ከተያዘው 39.55 ቢሊዮን ብር፣ 42.29 ቢሊዮን ብር በመሰብስበ የዕቅዱን 106.95 በመቶ ማሳካት ተችሏል።ይህ አፈጻጸም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 10.85 ቢሊዮን ብር ወይም 34.48 በመቶ ብልጫ አለው።

**አዲስ ዘመን፡- የስድስት ወራት የገቢ ዕቅድና አፈጻጸም ስኬታማነት አስተዋፅኦ ያደረገው ምንድ ነው? ስውጤቱ ያበቃችሁ ምን እንደሆን ገምግማችኋል?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** ቢሮው በስድስት ወር ለመሰብሰብ በዕቅድ ከተያዘው 39 ነጥብ 55 ቢሊዮን ብር፣ 42 ነጥብ 29 ቢሊዮን ብር በመሰብሰብ የዕቅዱን 106 ነጥብ 95 በመቶ ማሳካት ችሏል።ይህ አፈጻጸም ካለፈው በጀት ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር 10 ነጥብ 85 ቢሊዮን ብር ወይም 34 ነጥብ 48 በመቶ ብልጫ አለው፡፡

ቢሮው የህግ ዘርፍ የበጀት ዓመቱን የገቢ ዕቅድ ለማሳካት ከአጋር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ በጋራ በመንቀሳቀስ፣ ግብርን በፍቃደኝነት የመክፈል ባህልን እንዲያድግ በማድረግ፣ ታክስ ከፋዩን ማህበረሰብ በልዩ ልዩ የግንኙነት አግባቦች በማስተማር፣ በመደገፍ እና እውቅና በመስጠት እንዲሁም የህግ ተገዥነትን በማሳደግ ለስድስት ወራቱ ዕቅድ ስኬት የበኩሉን ሚና ተወጥቷል፡፡

ከሞደርናይዜሽን ሥራዎች አኳያም ቢሮው የተገልጋዩን እርካታ በላቀ ደረጃ ለማረጋገጥ የግብር ክፍያን የተለያዩ የቴክኖሎጂ አማራጮችን እየተጠቀመ ነው።እስካሁን ተቋሙ የሲ.ቢ ኢ፣ የቴሌ ብር እና የ7075 የውስጥ የስልክ መስመሮችን በመጠቀም ፈጣን መስተንግዶ መስጠት ከማስቻሉ ባለፈ የብልሹ አሰራር መንስኤዎችን ለመቀነስ ዓይነተኛ ሚና ተወጥቷል።ይህም ለስድስት ወሩ የዕቅድ ስኬት አስተዋፅኦ ነበረው።የታክስ ስራዎች በተመለከተም ቢሮው በታክስ ዙሪያ ግብር ከፋዩ የነቃ ግንዛቤ ይዞ ግብሩን በወቅቱ እንዲከፍል በኦዲት፣ በገቢ ሂሳብ እና በተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ ሰፊ ስራዎች

# ተጠየቅ



**ያለ ንግድ ፈቃድ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎችም የቢሮውና የከተማዋ ፈተና መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ከንግድ ቢሮ ጋር በመነጋገር ወደ ታክስ መርህ እንዲመጡ እያደረግን ነው**

በቅድም ሁኔታ መሰራታቸው ለገቢ መጨመርና ለዕቅዱ መሳካት ጉልህ ድርሻ አብርክቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ቢሮው የባለጉዳዮችን ቅሬታ ለመፍታት ብሎም በፍጥነት ለማስተናገድ ቴክኖሎጂን ከመጠቀም አኳያ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የገቢውን አቅም ለማሳደግ አንዱና ትኩረት የሰጠው ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም ነው።በቴክኖሎጂ የተደገፉ ስራዎች የድምር ውጤታቸው የተሻለ እንደሚሆን እናምናለን።በተለያዩ አግባቦችም ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ነው የምንሠራው።ቴክኖሎጂ ሁኔታዎችን ጊዜ እና ገንዘብን ከመቆጠቡም በተጨማሪ አሰልቺ አሰራሮችን ለመቅረፍ ይጠቅማል። ቴክኖሎጂ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያዘለ ነው።በተለይም ብልሹ አሰራሮችን በመቅረፍ ረገድ ቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ የለውም።ይህም በመሆኑ በቴክኖሎጂ ላይ ትልቅ ትኩረት አድርገናል።

ለምሳሌ ግብር ከፋዮች ከአንድ በላይ አካውንት ሊኖራቸው ስለሚችል ብዙ አማራጮችን ተጠቅመናል።ይህም የግብር ከፋዮችን ምቾትና ፍላጎት ለመጠበቅ ስንል ከሀገራችን ካሉ አስራ ስድስት ባንኮች ጋር እንደ አስፈላጊነቱ እየሠራን ነው።ይህም በመሆኑ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን እያገኘን ነው።

ከኢትዮ- ቴሌኮም ጋርም በመነጋገር አስፈላጊ የሚባሉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች በመጠቀም ደንበኞቻችን ላይ የምንሰበስበውን ግብር ለማሳካት ጥረት እያደረግን ነው።ከዚህም በተጨማሪ 7075 ደንበኞች በማንኛውም ጊዜ መረጃ የሚያገኙበት አጭር መስመር ጥቅም ላይ አውለናል።በዚህ መስመር የሚፈልጉትን ጥያቄ ማንሳት ይችላሉ።በቂ ማብራሪያ የሚሰጣቸው ይሆናል።ይህ ለደንበኞቻችን ብቻ ሳይሆን ስለተቋሙ የተለያዩ አሰራሮችን እና ተግባራትን ለማወቅ ለሚሹ አካላትም ትልቅ ፋይዳ እየሰጠ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ተቋም በባህሪው ከፍተኛ ገንዘብ የሚሰበስብ ነው።ለሙስና ቀዳዳ የሚከፍቱ አሰራሮችም አሉ። በዚህ በኩል አመራሮችና ባለሙያዎች ለሙስና እንዳይጋለጡ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** ቢሯችን ሙስናን በመዋጋት ረገድ ከአመራር እስከ ሰራተኛ በተናበበ መንገድ ይሰራል።ሙስና ማለት የአንድ ሀገር የዕድገት ፀር ነው።ይህም በመሆኑ በዚህ ላይ ትልቅ ትኩረት ነው የምንሰጠው።ይሁንና ግን አሁንም ሙሉ ለሙሉ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን አስቀርተናል ማለት አይቻልም። ሆኖም ተቋማችን ይህን ለማስቀረት ትኩረት ሰጥቷል፡፡

ለአብነትም በጎ ግብር ከፋይ እና በጎ ባለሙያ ማፍራት አለብን በሚል በስፋት እየሰራን ነው።ይሁንና በተለያዩ ወቅቶች አግባብነት የጎደለው ተግባር ላይ የሚሳተፉ አካላትን እያገኘን ነው።በዚህ ላይ የተገኙት ላይ ደግሞ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ቀጥለናል፡፡

በዚህ ዓመት እና ባለፈው ዓመት ከዚህ ጋር በተያያዘ 260 ባለሙያዎች ላይ እርምጃ ወስደናል።እርምጃው የየራሱ ሂደት እና ህጋዊ አግባብ ያለው ነው።ይህም እስከ ሥራ ማባረር የደረሰ እርምጃ ነው የተወሰደው ።ይህ ግን ሙሉ ለሙሉ ችግሩን ለመቅረፍ አስችሎናል ብለን አንቀመጥም።ብዙ መሠራት ያለባቸው ሥራዎች አሉ።ግብር በባህሪው ብዙ ገንዘብ የሚንቀሳቀስበት እና ባለጉዳዮችም በርካቶች ስለሆኑ መሰል ድርጊቶች እንደሚኖሩ ታሳቢ አድርገን በጥንቃቄ እንሰራለን።ባለሙያዎችም ሆኑ አመራሮች ከመሰል ድርጊቶች እንዲታቀቡ በየጊዜው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንሰራለን። በተጨማሪም የድጋፍ እና ክትትል ስራችንም በተጠናከረ ሁኔታ የሚካሄድ ነው የሚሆነው።በውስጣዊ አሰራሮችም ጠንካራ ዲስፕሊን እንከተላለን፡፡

ሙስና እና ብልሹ አሰራር በባለሙዎች ብቻ የሚገለፅ በዚያው የተወሰነ አይደለም።ስለዚህ ከግብር ከፋዮች አኳያም 1000 ግብር ከፋዮች ላይ ደግሞ አስተዳደራዊ እርምጃዎች ተወስዶባቸዋል። ከዚህ አለፍ ብሎ ወንጀል ፈጽመው የተገኙትን ደግሞ ከከተማው የፍትህ አካላት ጋር በመሆን ክስ የመመስረት እና በህግ አግባብ ብይን የሚሰጥበት ሂደት አለ።በአሰራር ሥርዓቱ መሰረትም ህግና ፍትህ የሚተገበር ይሆናል ፡፡

በአጠቃላይ ግን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የከተማዋም ሆነ የሀገሪቱ ፈተና በመሆኑ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራው ጉዳይ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ከፍተኛ ግብይት ከሚፈፀምባቸውና ግብር ስወራ ከሚካሄድባቸው አካባቢዎች አንዱ መርካቶ ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ይነገራል። ይህ ችግር አሁን ተቀርፏል?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** በመርካቶ አካባቢ የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች አሉ። በዚህ ገበያ ሰፋ ያለ ነገር አለ።በህገ ወጥ መንገድ ሲሰሩ የነበሩትን ወደ ህጋዊ መንገድ እንዲመጡና ህጋዊ የሆኑ አካላት ደግሞ እንዲበረታቱ በስፋት ሰርተናል።በዚህም 35 ሺህ የሚደርሱ ግብር ከፋዮች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው እንዲሰሩ አድርገናል።እነዚህን ተግባራት ስናከናውን ከሚመለከታቸው የፌደራል እና የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የመጣ ነው።በከተማ ካሉን ሁሉም ቅርንጫፎች እና ንዑስ ቅርንጫፎች ጋር በመነጋገር እና በመናበብ የመደጋገፍና ክትትል ሥራ እያከናወንን ነው፡፡

በመርካቶ አካባቢ ግን ብዙ በችግር የሚነሱ ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው በጣም ሊበረታቱ እና ሊደነቁ የሚገቡ ጉዳዮችም መኖራቸውን ማስተዋል አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- እስኪ ሊበረታቱ እና ሊደነቁ የሚገቡ ያሏቸውን በማሳያነት ይንገሩን ?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** በዚህ አካባቢ በጣም ከፍተኛ የሆነ የቢዝነስ እንቅስቃሴ አለ።ነገር ግን በመርካቶ የምናገኘው ቢዝነስ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የሆነ የህዝብ መስተጋብር ያለበት ስፍራ ነው።የኢትዮጵያን ስብጥር ቀለም የምንመለከትበት የግብይትና የመኖሪያ ሰፈር ጭምር ነው። ይህን እሴት መንከባከብና ወደ ተሻለ መስመር ማስገባት ይጠበቅብናል።መርካቶ ላይ ያለውን መልካም መስተጋብር በማጠናከርና ዘመናዊ በሆነ መንገድ በመከተል ማስቀጠል ተገቢ ነው።

መርካቶ አካባቢ መሠራት ያለበት የቀድሞው ሙሉ ለሙሉ በአዲስ አሰራርና መንገድ መተካት ወይንም ደግሞ ሌላ ገፅ ለመስጠት ሳይሆን በቴኖክሎጂ እና ህጋዊነት መስመርን በተከተለ መንገድ ወደ ህጋዊ መስመር ማስገባት ነው። ይህን ሥራ በአሁኑ ወቅት ጀምረናል።ከዚህ አኳያ ከዚህ ቀደም ግብር ከፋይ የነበሩት 20ሺ የሚበልጡ አልነበሩም።ይሁንና ባለፈው ዓመትና በዚህ ዓመት ሰፊ የንቅናቄ ሥራ በመስራታችንና ግንዛቤ በመፈጠሩ በአሁኑ ወቅት 35ሺ ግብር ከፋዮች ተገኝተዋል።ሆኖም መርካቶ ውስጥ ካለው የቢዝነስ እንቅስቃሴ አኳያ ይህም በቂ አይደለም።በመሆኑም በሚቀጥለው ይህን አሰራር የማዘመንና የሚሰበሰበውን ግብር በማሳደግ ውጤታማ ማድረግ አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ እስካሁን ያልተሻገራቸው ፈተናዎች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ በየጊዜው የተሻሻሉ አሰራሮችን በመተግበር ላይ ይገኛል።በዚህም ደንበኞቹን ፍላጎት ለመጠበቅ እየሠራ ሲሆን በርካታ ለውጦችም እያየን ነው።ይሁንና አሁንም ድረስ መስተካከል ያለባቸውና ያልተሻገርናቸው ችግሮች አሉ።

ሀሰተኛ ደረሰኝን በሚመለከት በተደጋጋሚ ሥራ ለመስራት ሞክረናል።ይሁንና አሁንም በመሰረታዊነት ተፈቷል ማለት አይቻልም።ይህ ትኩረት የሚሻና በርካታ ባለድርሻ አካላትን ጥረት የሚጠይቅ ነው።ሌላው ከተሸጠው ዕቃ በማሳነስ ዋጋ መፃፍና መንግስት ማግኘት ያለበትን ጥቅም የመሰወርም ችግር አለ።ይህን ችግር ለማቃለል ከሚመለከታው አካላት ጋር መስራትና ርብርብር በማድረግ ውጤት ማምጣት ይቻላል፡፡

ከሸማቾች አኳያም አሁንም ችግሮች ይስተዋላል። የሸማቾችም ደረሰኝ የመጠየቅ ባህል አልዳበረም።ይህን እሳቤ ለማጠናከር እና ደረሰኝ የሚጠይቁትንም የማበረታታት ሥራ መጀመር ይገባል።

በኢ-መደበኛ ሁኔታ የተደራጁና ግብር የማይከፍሉ ነጋዴዎች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ፈተና ነው።ያለ ንግድ ፈቃድ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎችም የቢሮውና የከተማዋ ፈተና መሆኑ መታወቅ አለበት። እነዚህን ችግሮች ለማቃለል ከንግድ ቢሮ ጋር በመነጋገር ወደ ታክስ መርህ እንዲመጡ እያደረግን ነው፡፡

ኢ-መደበኛ ነጋዴዎችን ህጋዊ የማድረግ ሥራ በትኩረት እየተሠራ ነው።ከንግድ ማህበረሰብ አኳያም እስካሁን ያልተፈቱ ችግሮች አሉ።በሚወጣው መርሐ ግብር መሰረት በወቅቱ መጥተው ግብር ማሳወቅና መክፈል ላይ ከፍተኛ መጓተት አለ።በርካቶቹ ግብር ከፋዮች የሚመጡት በመጨረሻው ሠዓት ነው።ይህ ሲሆን ሥራው ላይ ጫና ይፈጥራል።ከዚህ በተጨማሪም ለብልሹ አሰራርም በር የሚከፍት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ ቀጣይ ትኩረት ምንድን ነው?**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** በመጀመሪያ አሁንም የሥነ ምግባር ግንባታ ሥራ ላይ በስፋት የሚሰራ ይሆናል።ሥራዎች ጥናትን መሰረት ያደረጉ መሆን እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል።ለግብር ከፋዮችም ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትኩረት አድርገናል።አገልግሎት አሰጣጣችን በተጠናከረ መንገድ ማስኬድና ሌላኛው የትኩረት ነጥብ ነው።ከዚህም በተጨማሪ የተገልጋዮችን ምቾት ለመጠበቅና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በስፋት የምንተገብርና የምንጠቀም ይሆናል፡፡

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ወደ ተግባር በማስገባታችን በግብር ከፋዩና በፈፃሚው መካከል የነበረውን ግንኙነት መቀነስ መቻሉ የሥነ ምግባር ጉድለቶችን ማሻሻል ተችሏል። በቀጣይም በመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት ወይንም ስድስት ወራት ዕቅድ አፈፃፀማችን ግምገማ በመነሳት የተገኙ መልካም ውጤቶችን በማስቀጠል የነበሩ ተግዳሮቶችን በአሠራር በመፍታት የቀጣይ የገቢ አሰባሰባችንን በላቀ ደረጃ በማሳለጥ ዕቅዳችንን ለማሳካት በቀሪው ጊዜ የበለጠ ውጤት ለማስመዝገብ እየሰራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበርዎት ቆይታ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ሙሉጌታ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "የትውልዴ እብደትና...

ከ5ኛ ገጽ የዞረ

"ይህ የዛሬው ትውልድ የት ላይ ነው ያለው? የድርጊት ትውልድ ነው ወይንስ ችኩል ትውልድ ነው? ጤነኛ ትውልድ ወይንስ ያበደ ትውልድ? ያቋራጭ ትውልድ ወይንስ የቀጥተኛው መንገድ ትውልድ? ፍትሐዊ ትውልድ ወይንስ ፊት አይቶ የሚያዳላ ትውልድ? የእንብላው ትውልድ ወይንስ የእንሥራ ትወልድ? ‹ሁሉን አውቃለሁ ባይ› ትውልድ ወይንስ የጥልቅ እውቀት ባለቤት ትውልድ? የጥበብ ትውልድ ወይንስ የመጠበብ ትወልድ? ሚዛናዊ ትውልድ ወይንስ ፅንፈኛ ትውልድ? ስሜታዊ ትውልድ ወይንስ አስተዋይ ትውልድ? የስብሰባ ትውልድ ወይንስ የውጤት ትውልድ? የፕሮፓጋንዳ ትውልድ ወይንስ የድርጊት ትውልድ? አጨብጫቢ ትውልድ ወይንስ ራሱን የሆነ ትውልድ? እህ ደከመኝሳ! እናንተም ጥያቄውን ጨምሩበታ...!" ይሉናል ጸሐፊው። እንኳንስ ልንጨምርበት የተዘረዘረውም ልባችንን ፍስስ ስላደረገ በምኑ ላይ ምን ይታከላል?!¡።

**የትውልዴ የወፈፍታ ምልክቶች፤**

እውነት እውነቱን እንመስክር ካልን አብረን "የሕይወትን ጽዋ" እየተጋትን ያለነው ይህ የዕድሜዬ ማሕበርተኛ ትውልድ እብደት ከቀዳሚ ዘመናት ትውልዶች የመጠን ከፍታ አሳይቶ ካልሆነ በስተቀር የመሻሻል ምልክት አሳይቷል ለማለት ያዳግታል። ጥቅል ፍረጃ እንዳልሆነ ልብ ይባልልኝ። በውሱንነት የምጠቅሳቸው የመከራከሪያ ነጥቦቼ አወዛጋቢ ቢመስሉም "እውነቱን ተናግሮ የመሸበት ማደሩ" የከበረ ብሂል መሆኑን ስለማምንበት እየጠዘጠዘን ያለውን ማሕበራዊ እባጭ ጨክኖ ማፍረጡ ለፈውሳችን ስለሚያግዘን ደፈር ማለቱ ክፋት ያለው አይመስለኝም። ቅዱስ መጽሐፍስ ቢሆን "ጆሮ ያለው ይስማ!" በማለት ይመክረን የለ። "ሕመሙን የማይናገር በሽተኛ ፈውሱ መጋኛ" የሚለው ሀገራዊ ምሳሌም ሃሳቤን ይደግፍ ይመስለኛል።

**አንድ፡-** ይህ የእኔ ትውልድ የሃሳብ ልዩነቱን ለማቀራረብ ከምክክር ይልቅ ጋሻና ጦር ይዞ ይዋጣልን እያለ የፍልሚያ ሽማ ቢጣጣል ይመርጣል። "የወንድሙ ጠባቂ" ከመሆን ይልቅ ወንድም እህቱን ማሳደድ የሚያረካው ይመስላል። ባለራእዮችን ከማድመጥ እና ሕልመኞችን ወደ ግብ ከማቃረብ ይልቅ የመሰናክል ድንጋይ እየደረደረ መንገዳቸውን መዘጋትን ምርጫው በማድረግ የሚፈነድቅም ይመስለኛል።

ጦርነትን ከባህላዊ እስክስታ እኩል እያስተያየ ሲፎክርም አቅሉም፣ ነፍሱም አይገስጹትም። የወገን መፈናቀልና መንከራተት "የብሔርና የቋንቋ ክብር መገለጫ" እንደሆነ፣ የብዙዎችንም ስደት "የአሸናፊነቱ" ምልክት አድርጎ በማየት ሲኩራራ ማስተዋል እብደት ካልተባለ በስተቀር ምን ሊባል ይችላል። ያውም ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰ የማንነት ቀውስ።

**ሁለት፡-** የትውልዴ መንፈስ በዘመን አመጣሹ ቴክኖሎጂ ተበክሎ ክፉኛ የታመመም ይመስለኛል። እስከ ዛሬ ድረስ መድኃኒት ያልተፈጠረለትና ወደፊትም ፈዋሽ መድሐኒት ሊፈጠርለት ይችላል ተብሎ ተስፋ የሚጣልበት አይመስልም ግሎባላይዜሽን ብዘውን የትውልዴን ሥራዊት ለእብደት ዳርጎ ሕመም ላይ የጣለው በአጭር ዓመታት ውስጥ ነው። ስማቸው ብዙ፤ ግብራቸው ተመሳሳይ በሆኑ "እሳት አቀጣጣይ፣ መርዝ ረጭ" የማሕበራዊ ሚዲያ ወረርሽኞች ያልተጠቃ ዜጋ ለማግኘት ብዙ ማሠሥ የሚያስፈልግ አይመስልም። አንድ ሰው እንዳሉት "አእምሮው በማሕበራዊ ሚዲያ በሚሠራጩ ክፉ መረጃዎችና ክፉቶች ያልተበከለ ዜጋ ማግኘት የሚቻለው ያልተወለዱ ጽንሶች ባሉበት የእናት ማህጸን ውስጥ ብቻ ነው።"

በአንድ እጁ ሞፈር በሌላ መዳፉ የእጅ ስልኩን በማሽሞንሞን "ምን ተባለ? ማንስ ምን ደረሰበት?" የሚሉ አልባልታዎችን ሲያሥሥ የሚውል የሀገሬ አርሶ አደር ቁጥሩ ቀላል የሚባል አይደለም። ከሕጻን እስከ አዋቂ፣ ከቤት እመቤት እስከ የቤተሰብ አጋዥ "ሠራተኛ"፣ ከምሁር እስከ ተማሪ፣ ከወታደር እስከ ወዝ አደር፣ ከነጋዴ እስከ "ምንግዴ" ሥራ ጠል፣ ከዳኛ እስከ ጠበቃ፣ ከወጣት እስከ ባለ ሽበት ወዘተ. ከላይ የጠቀስነው ጸሐፊ "እህ! ደከመኝሳ!" ብሎ ጽሑፉን እንደደመደመ ሁሉንም ዘርዝሮ ለመጨረስ ልብ ያደክማል።

ከላይ የተዘረዘሩትም ሆኑ ሳናስታው ሳቸው የዘለልናቸው በርካታ የማሕበረሰቡ ቤትኞች በማሕበራዊ ሚዲያው የሚጠቀሙት በእርግጡ አዎንታዊ ጠቃሚ መረጃዎች አጓጉተዋቸው ነው ወይንስ ለሌላ አሉታዊ መሻት? ጠቅላይ ምላሽ ለመስጠት ተገቢውን ጥናት ማድረግ ግድ ስለሚል አንባቢያን የራሳቸውን ግምት ቢሰጡ ይበልጥ የተሻለ ይሆናል። በቅርቡ የሜታ (ፌስ ቡክ) ኩባንያ "የኢትዮጵያዊያን የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም አሉታዊ ገጽታው እየሰፋ ስለሆነ በእጅጉ አሳስቦኛል" በማለት ያወጣው ሪፖርት እንደ ሀገር ዘመኔንና ትውልዴን በሚገባ የሚገልጽ ይመስለኛል።

"በአሉታዊዎቹ ላይ ከማተኮር ይልቅ ስለምን ደግ ደጉን የማሕበራዊ ሚዲያ ጥቅም አትዘረዝርም!?" ተብሎ እንደሚጠየቅ አይጠፋኝም። ለዚህ ከስ የማቀርበው መከራከሪያ ከአሁን ቀደም የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማችንን በተመለከተ "በረከተ መርገም" በማለት ያቀረብኩት ጽሑፍ የጠቀሜታውን ብርታትና የአሉታዊ ስፋቱን ልክ የዳሰሰ ስለሆነ ተመልሼ አልከልሰውም። ሞጋቾቼ ያንን ጽሐፍ መለስ ብለው እንዲያነቡ እመክራለሁ።

በጥቂቱ ለማስታወስ ካስፈለገ ግን ከዘመን ጋር መኳረፍም ሆነ መጣላት እንደማይቻል ይገባኛል። የማሕበራዊ ሚዲያ በጎነትም አይጠፋኝም። ያለ እርሱ ኑሮን እንግፋ ማለቱም "ወደ ጥንታዊ የጋርዮሽ ሥርዓት እንመለስ" የማለት ያህል ነው። እኔው ራሴም ብሆን የማሕበራዊ ሚዲያው ተጠቃሚ መሆኔን አልክድም። መሟገቻዬ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ አስገብሮናል፣ ሳናውቅ አዋቂ እንድንመስል እየቀረጸን ነው፣ መልካም ሥነ ምግባርን የሚያዋርዱ፣ ሃይማኖትን የሚያረክሱና ጎሊናን የሚያቆሽሹና ሰብእናን የሚያዋርዱ አረሞች ወረውናል።

ልጆቻችን በአደገኛ ሱሱ ተማርከው ከእጃችን እያመለጡን ነው። አብዛኞቹ የማሕበራዊ ሚዲያው ተጠቃሚዎች በሚገባቸውም ሆነ በማይገባቸውም ርዕሰ ጉዳዮች ዋና ተንታኝ፣ ተቺና ተሳዳቢ ወደመሆን መለወጣቸውን ስናያ እየዘንን ዘመኑን መኮነናችን አልቀረም። ሁላችንም እንዳሻችን እንድንፈነጭ መድረኩ በሠይጣናዊ ክህነት አርክሶናል ለማለትም ይቻላል። ይህ የእብደት ጥግ ተደርጎ ካልታየ ሌላ ምን ማሳያ ሊኖር ይችላል።

**ሦስት፡-** የሰላምና የፍቅር ተምሳሌት ተደርጎ የሚታመነው ነገረ ሃይማኖት የጠብና የሙግት፣ "የይዋጣልን" አጀንዳ ማራመጃ፣ የመከባበሪያና የመጽናኛ መልእክት ሳይሆን የዛቻና "የቆይ ጠብቀኝ!" መፎከሪያ ሆኖ ስናስተውል "አብደናል" ከማለት ውጭ ምን ማለት ይቻላል። ቅዱስ ወንጌሉን ለወንጀል፣ የተከበረው ቁርዓን ለማጥቂያ እንዲውል ማድረግ በምድርም ብቻ ሳይሆን በተስፋ በሚጠበቀው የሰማይ ቤት ጭምር የሚያስጠይቅ የከፋ ኃጢያት መሆኑ መዘንጋቱ ለእብደታችን ዋና መንስዔ ነው ቢባል አገነናችሁ ያሰኛል?

**አራት፡-** ፖለቲካችን ወፍፎ እኛን ዜጎችን ካወፈፈን ዓመታት ተቆጥረዋል። ኢኮኖሚው ጨርቁን ጥሎ ካበደ ሰነባብቷል። ማሕበራዊ ተራክቧችን ስንጥቁ እየሰፋ መሄድ ከጀመረም ቆይቷል። "እህ ደከመኝሳ! እናንተም ጨምሩበታ...!" እንዳለው ጸሐፊ ይህ አምደኛም ብእሩም ልቡም ድክም ማለቱ አልቀረም።

ዛሬ የምንዘራውና ለእብደት የዳረገን ክፉ ዘርፈ ብዙ ማሕበራዊ አረም በአጭሩ ተቀጭቶ መረጋጋት እስካልተቻለ ድረስ ጦሱ በዚህ ትውልድ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይሆንም። እብደቱ ወደ ነገው ትውልድም ተሸጋግሮ ኢትዮጵያችን "በአእምሮ ሕሙማን ሆስፒታልነት" እንዳትፈረጅ ልባችን ልብ ሊገዛ ይገባል። በቁጣና በቂም የጋለው መንፈሳችን ቀዝቅዞ ይስከን። ለበቀል የተመዘዘው ሰይፋችንና ለጥፋት ያነጣጠረው የጠብመንጃ መሣሪያችን ቁልቁል ይዘቅዘቅ። ሰላም ለሀገራችን፤ ለዜጎችም በጎ ፈቃድ!

"ሩጫ ላይ ያለች ሀገር ናት፡፡ ቢከፋም ቢስማም ድርጊት! አዲሱ ትውልድ የድርጊት ትውልድ ነው፡፡ ጊዜ ያጥረናል፣ ጊዜ የለንም፣ ችኩል ትውልድ ነን፡፡ ያበደ ትውልድ፡፡ እውነት እብዶች ነን! ያሮጌው ትውልድ ሙጣጭ፤ ያዲሱ ትውልድ የበኩር ልጅ፡፡ ያንዱ መጨረሻ፤ የሌላው መጀመሪያ መሆን እብደት ነው። ያሮጣል...ንግግር! ንግግር! ንግግር! የጊዜያችን ምልክት ነው፡፡ ብዙ ንግግር ትንሽ ሥራ፡፡ የለም! ሌሎች ደግሞ ከስብሰባ ጋር ያያይዙታል፡፡ ስብሰባ! ስብሰባ! ግምገማ! ግምገማ! ብዙ ስብሰባ፣ ብዙ ግምገማ ትንሽ ውጤት" (ገጽ 13 እና 48)

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# የሲሚንቶ ነጋዴዎችን፣ ጫኝና አውራጆችን ወደ ስራ የመለሰ አሰራር

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ሀገሪቱ የሰሚንቶ ዋጋ እየናረ መጥቶ ለግንባታው ዘርፍ ትልቅ ፈተና እስከመሆን ደርሶ እንደነበር ይታወሳል።መንግሥትም ይህን የሲሚንቶ ዋጋ ለማረጋጋት በተደጋጋሚ የተለያዩ እርምጃዎች ሲወስድ ቆይቷል፤ ይሁንና ዋጋውም አልቀመስ ብሎ መቆየቱም ይታወሳል።

የሲሚንቶ ዋጋ በከፍተኛ መጠን ማሻቀብ ብቻም አልነበረም ችግሩ።ምርቱ በገበያው ሊገኝ አለመቻሉም ሌላው ፈተና ነበር።መንግስት በሲሚንቶ ላይ ቁጥጥር ለማድረግ የወሰደው እርምጃም ሌላ ችግር አስከትሏል፤ የኬላ መብዛትና ሲሚንቶ ይዞ መንቀሳቀስ ፈታኝ ሆነው ነበርና።መንግስት ለግዙፍ ፕሮጀክቶች ምቹ ሁኔታ ቢፈጥርም፣ ሌሎች ፕሮጀክቶችና ትናንሽና ቀላል ግንባታዎች ምርቱን በገበያው ላይ እንደልብ ማግኘት አለመቻላቸውን ተከትሎም ግንባታ የተቀዛቀዘበት ሁኔታ ታይቷል።

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ መንግሥት ሲወስዳቸው የነበሩ የመፍትሔ አማራጮች የዘርፉን ችግር በዘላቂነት መፍታት አልቻሉም።መፍታት አለመቻል ብቻም ችግሩ ይበልጥ እየተወሳሰበ ነው የመጣው።ሲሚንቶ የመልካም አስተዳደር ችግር ምንጭ መሆኑ እየተጠቀሰም ቅሬታዎች ይነሱበትም እንደነበር ይታወቃል።

ይህን ሁሉ ተከትሎም መንግስት ከአንድ ወር በፊት ወደሌላ እርምጃ ገብቷል።ቀደም ሲል በሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት ላይ ያወጣውን መመሪያ በማሻሻል የገበያ ስርዓቱን ቀድሞ ወደነበረበት በመመለስ ሲሚንቶ በነጻ ገበያ እንዲመራ የሚያስችል ውሳኔ አሳልፏል።በዚህም መሰረት የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭትን ለመቆጣጠር የወጣው መመሪያ ቁጥር 908/2014 ተሽሮ መመሪያ ቁጥር 940/2015 እንዲጸድቅ ተደርጎ አዲስ ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ወደ ስራ ተገብቷል።በአሁኑ ወቅትም ሲሚንቶ ለገበያ እየቀረበ ያለው በዚህ መመሪያ መሰረት ነው።

በውሳኔው መሰረትም የሲሚንቶ ገበያ፤ “በነጻ ገበያ” እንዲመራ ሆኖ በየአካባቢው የሚኖረውን የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ የመወሰን ኃላፊነትም ለፋብሪካዎች ተሰጥቷል። ከዚህ በተጨማሪም፤ በፋብሪካዎች እና ተጠቃሚዎች መካከል ያሉት አከፋፋዮች እና ቸርቻሪዎች ከሲሚንቶ ግብይት እና ስርጭት እንዲወጡ ያደረገውን አሰራር የቀለበሰ ሆኗል።

ውሳኔው መተግበር በጀመረባቸው ሰሞናት በዚህ ገጽ በሰራነው ዘገባ ያነጋገርናቸው የግንባታ ተቋራጮች ሲሚንቶ ገበያ ላይ መታየት መጀመሩን፣ ዋጋውም ቅናሽ ማሳየቱን ገልጸውልን ነበር።ሲሚንቶ በነጻ ገበያ መሸጥ መጀመሩ ቀደም ሲል ጭር ብለው የሰነባበቱ የሲሚንቶ መሸጫ አካባቢዎች ሞቅ ደመቅ እንዲሉ እያደረጋቸው መሆኑንም ደግሞ ሰሞኑን ገበያዎቹን ተዘዋውረን በተመለከትንበት ወቅት ማረጋገጥ ችለናል፡፡

በእያንዳንዱ የሲሚንቶ መሸጫ አካባቢ ምርቱ ሲወጣና ሲወርድ እየታየ ነው።ነጋዴዎቹም አቅርቦት መኖሩን ተከትሎ ሱቆቻቸውን ከፍተው እየሰሩ መሆናቸውን አረጋግጠውልናል።በአካባቢዎቹ በሲሚንቶ ጫኝና አውራጅነት የሚሰሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ስራቸው እንደተመለሰላቸው ነው የገለጹት።

አቶ አስቻለው ተካ አዲስ አበባ ውስጥ ጀሞ ቁጥር ሶስት ፉሪ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲሚንቶ በችርቻሮ በመሸጥ ይተዳደራሉ። መንግሥት ከዚህ ቀደም በሲሚንቶ ገበያው ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ያስችላል በሚል አውጥቶት የነበረው መመሪያ ሲሚንቶ ቸርቻሪዎች ሲሚንቶ እንዳይገዙ እና እንዳይሸጡ የሚያደርግ እንደነበር ያስታውሳሉ፤ በወቅቱ እርሳቸው እና መሰል ቸርቻሪዎችን ብቻ ሳይሆን ገዢዎችም ጭምር እጅግ ተጎድተው እንደነበር ነው የሚገልጹት። መመሪያው በወጣበት ወቅት አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ከሁለት ሺ ብር በላይ ሲሸጥ እንደነበረ ተናግረዋል።

በቅርቡ መንግሥት ሲሚንቶ በነፃ ገበያ እንዲመራ በሚል ያስተላለፈውን መመሪያ ተከትሎ በሦስት እና በአራት ቀናት ውስጥ ዋጋው መሻሻል ማሳየቱን በመጥቀስ፤ አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ከአንድ ሺ እስከ አንድ ሺ 500 እንዲሁም አንድ ሺ 700 ድረስ ወርዶ መሸጥ ጀምሯል ሲሉ ያመለክታሉ። በጅምላ ለሚገዙ ደግሞ ዋጋው ከዚህም በላይ እንደሚቀንስ ነው የጠቆሙት።

እርሳቸው እንዳሉት፤ እርሳቸውም ሆኑ ሌሎች የሲሚንቶ አከፋፋዮች ኢትዮጵያ ውስጥ በቂ የሲሚንቶ ምርት እንዳለ ያምናሉ፤ በመሆኑም ዋጋው ከዚህ በታች ይወርዳል የሚል ተስፋ አላቸው። ለዚህም ሲሚንቶ ፈላጊ ደንበኞች ተረጋግተው እንዲጠባበቁና እጅግ አስቸኳይ ለሆነ ግንባታ ካልሆነ በስተቀር ተስገብግቦ መግዛት ተገቢ እንዳልሆነና መረጋጋት እንደሚያስፈልግ ይመክራሉ።

በመገናኛ አካባቢ ከሚገኙና ሲሚንቶን በችርቻሮ ከሚሸጡ ነጋዴዎች መካከል አቶ ትንሳኤ ክብሩ አንዱ ናቸው። እሳቸውም በጀሞ ቁጥር ሶስት ፉሪ አካባቢ ሲሚንቶ በችርቻሮ በመሸጥ እንደተሰማሩት አቶ አስቻለው ሁሉ፤ በአሁኑ ወቅት ያለውን የገበያ ሁኔታ የተሻለ ሲሉ ይገልጹታል፡፡

መንግሥት የዛሬ አንድ ወር አካባቢ በሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት ላይ ያሳለፈው መመሪያ ማለትም የሲሚንቶ ገበያ በነጻ ገበያ እንዲመራ መፍቀዱ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ይገልጻሉ።እንደ አቶ ትንሳኤ ገለጻ፤ ከዚህ ቀደም አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ከ1800 እስከ 2000 ብር ይሸጥ ነበር።ምርቱም እንደልብ አይገኝም ነበር፤ አሁን ያለው የገበያ እንቅስቃሴ ጥሩ የሚባል ነው፡፡

ገበያውን ከዚህ በበለጠ ማረጋጋት እንደሚቻል አቶ ትንሳኤ የጠቆሙት።ለዚህም ከዚህ ቀደም የችርቻሮ ነጋዴዎች በቀጥታ ምርቱን ከፋብሪካ ማውጣት የሚችሉበት መንገድ እንዲመቻች ነጋዴዎቹ ተሰባስበው መጠየቃቸውን አስታውሰዋል።ላቀረቡት ጥያቄ ምላሽ ማግኘት ያልቻሉ ቢሆንም፣ የሲሚንቶ ግብይት በመንግሥት ቁጥጥር ውስጥ ከነበረበት ጊዜ ይልቅ አሁን የተሻለ ነው ሲሉ ያብራራሉ።በአሁኑ ወቅትም ሲሚንቶ በመንግሥት ቁጥጥር ውስጥ ከመግባቱ አስቀድሞ በነበረው የገበያ ሥርዓት ማለትም በነጻ ገበያ እየተመራ መሆኑን አብራርተው፣ ይህ በመሆኑም ገበያው እየተረጋጋ ይገኛል ብለዋል።

የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት ዙሪያ ያለው ችግር ዘርፈ ብዙ እንደነበር አቶ ትንሳኤ ያመለክታሉ።በሲሚንቶ ግብይት ስርዓት ውስጥ የተፈጠረው ችግር በርካታ በዘርፉ ተሰማርተው ሕይወታቸውን ይመሩና ቤተሰብ ያስተዳድሩ የነበሩ ነጋዴዎች ከመስመር እንዲወጡ ያደረገ እንደነበር በማስታወስም፣ አሁንም ድረስ ወደ ቀድሞው መስመር ለመግባት የተቸገሩ ነጋዴዎች ስለመኖራቸው አቶ ትንሳኤ ያመለክታሉ።የተወሰኑ የሲሚንቶ መሸጫ ሱቆች ዛሬም ድረስ መዘጋታቸውን ጠቅሰው፣ ምክንያቱ የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያው ያስከተለው ችግር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

የሲሚንቶ ፋብሪካዎች የሚያቀርቡት የሲሚንቶ ምርት ዋጋ የሚለያይ መሆኑን ያነሱት አቶ ትንሳኤ፤ አሁንም ቢሆን የተጋነነ ዋጋ በማቅረብ ገበያውን የሚረብሹ አንዳንድ ፋብሪካዎች ስለመኖራቸው ጠቁመዋል።ለአብነትም ሀበሻ ሲሚንቶ ነጋዴውን አስገዳጅ ወደሆነ መንገድ ውስጥ በመግፋት ተጨማሪ ክፍያ እየጠየቁ እንደሆነ ነው የተናገሩት።በአሁን ወቅትም ቀድሞ የተከፈለ ክፍያ ላይ ጭምር ተጨማሪ ዋጋ ካልተከፈለ ሲሚንቶውን እንደማይሰጡና አቅራቢውን አስገዳጅ በሆነ ውል እያሰሩት እንደሆነ ነው የገለጹት።በዚህም መሰረት አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ከፋብሪካው ሲወጣ ከ1000 እስከ 1100 ብር ድረስ እየጠየቁ እንደሆነም አንስተዋል።

ከፋብሪካው በ1000 እና 1100 ብር የወጣ አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ደግሞ አቅራቢው ወይም ኤጀንቱ የራሱን ድርሻ ጨምሮ እንዲሁም የትራንስፖርትና ሌሎች ወጪዎችን ጨምሮ ቸርቻሪው ጋር ሲደርስ ዋጋው የተጋነነ ይሆናል።ለዚህም ፋብሪካዎች በተመጣጣኝና ተመሳሳይ በሆነ ዋጋ ቢያቀርቡ መልካም ነው በማለት ሀሳባቸውን የገለጹት አቶ ትንሳኤ፤ ቀድሞ በተከፈለ ክፍያ ተጨማሪ ክፍያ መጠየቅ ተገቢ አለመሆኑን እንደ ችግር ጠቅሰዋል፡፡

በሲሚንቶ ገበያ ውስጥ የቆየውን ችግር ለመቅረፍ መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን ሲያቀርብ መቆየቱን ያስታወሱት አቶ ትንሳኤ፤ ነጋዴዎችም በበኩላቸው መፍትሔ ያሉትን ሃሳብ ሲጠቀሙ እንደነበር ጠቅሰዋል። በዚህም መሰረት ነጋዴዎች በማህበር ተደራጅተው አክሲዮን ማህበር በማቋቋም ነጋዴው ከፋብሪካው ጋር ትስስር በመፍጠር በቀጥታ መግዛት የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ጠይቀው እንደነበር ይገልጻሉ።ይህ አይነቱ አሰራር ቢፈቀድ በሲሚንቶ ገበያ ውስጥ ያለውን ችግር በዘላቂነት መፍታት እንደሚችል ነው ያመላከቱት፡፡

ሲሚንቶ በችርቻሮ የምትሸጠው ሌላኛዋ ነጋዴ ትዕግስት ታደሰም በተመሳሳይ አሁን ያለው የገበያ እንቅስቃሴ የተሻለ እንደሆነ ነው የገለጸችው።ባለፉት ጥቂት ወራት ምንም አይነት የሲሚንቶ ምርት ማግኘት ባለመቻሏ መሥራት እንዳልቻለች በማስታወስ፤ አሁን ላይ በመጠኑም ቢሆን ምርቱን እያገኘች መሸጥ መቻሏ ትልቅ ለውጥ እንደሆነ ነው ያነሳችው።

ባለፉት ወራት የአካባቢው የሥራ እንቅስቃሴ እጅግ ተቀዛቅዞ የነበረው ከምርት አቅርቦት እጥረት በተጨማሪ ሲሚንቶውን በመንግሥት ቁጥጥር ስር ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ነበር የሚል እምነት እንዳላት የገለጸችው ትዕግስት፤ አሁን ያለው የገበያ ሁኔታ ጥሩ እንደሆነና ምንም ካለመሥራት አሁን የተሻለ ነው ትላለች።

ለወራት ምንም የሲሚንቶ ምርት ማግኘት ባለመቻሉ ከሥራ ውጭ እንደነበረች ጠቅሳ፣ አሁን በመጠኑም ቢሆን እያገኘች መሆኑን ተናግራለች።አጠቃላይ የሲሚንቶ ዋጋ እንደየደረጃው የሚለያይ መሆኑን በመጥቀስም አንድ ኩንታል ሲሚንቶ ከ1500 እስከ 1600 ብር ድረስ እየተሸጠ መሆኑን ጠቅሳለች።ይህ ለውጥ የመጣው መንግሥት ከገበያው ውስጥ እጁን በማውጣቱና የሲሚንቶ ገበያ እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ በነጻ ገበያ እንዲመራ በመፈቀዱ ምክንያት ነው ብላለች፡፡

ባለፉት ወራት ነጋዴውን ጨምሮ ጫኝ አውራጆች ሁሉ ሥራ ፈት ሆነው ሲማረሩ እንደነበር በማስታወስ አሁን ሁሉም እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ብላለች።ደንበኞችም በጣም ተቸግረው ነበር ያለችው ትእግስት፣ በውድ ዋጋም ለመግዛትም ችግር እንደነበር አስታውሳለች።በአሁኑ ወቅት ሲሚንቶ ካለፈው ጊዜ በተሻለ ዋጋ እየተሸጠ እንደሚገኝ፣ ምርቱ ግን አሁንም በሚፈለገው መጠን እየቀረበ አለመሆኑን ጠቁማለች።የሲሚንቶ ምርት በሁሉም ሱቆች እንደሌለ ጠቅሳ፣ ሁሉም ነጋዴ እያገኘ እንዳልሆነ ነው ያመለከተችው።

ሲሚንቶ በማውረድና በመጫን ሥራ የተሰማራው ወጣት ቸርነት ታከለ፤ በመገናኛ አካባቢ ለረዥም ጊዜ እንደቆየ በመግለጽ፤ አንድ ኩንታል ሲሚንቶ በሰባት ብር ከሃምሳ ሳንቲም ሂሳብ የሚያወርድና የሚጭን መሆኑን ተናግሯል።በዚህ ሥራ በቆየበት ጊዜም አንድ ኩንታል ሲሚንቶ እስከ ሶስት ሺ ብር ሲሸጥ መመልከቱን ይናገራል።ነጋዴዎች የምርት አቅርቦት ሲገጥማቸውና መሸጫ ሱቆቻቸው ሲዘጉ እሱን ጨምሮ መሰሎቹ የዕለት ጉርስ ተቸግረው እንደነበርም አስታውሷል።

በጀሞ ቁጥር ሶስት ፉሪ አካባቢ ሲሚንቶ በመጫንና በማውረድ የሚተዳደረው ወጣት ታሬ ገመቹስ በበኩሉ በቅርቡ የሲሚንቶ መሸጫ ሱቆች እየተከፈቱ ሲሚንቶም እየመጣ ነው ይላል።በዚህም ደስተኛ መሆኑን ጠቅሶ፤ የሲሚንቶ ችግር ሲሚንቶ መሸጫ ሱቆቹን እስከመዘጋት አድርሷቸው እንደነበር ያስታውሳል።ሱቆቹ በመዘጋታቸው ምክንያት እሱን ጨምሮ ሌሎች አብረውት የሚሰሩ ወጣቶች ሥራ ፈተው መቆየታቸውን አስታውሶ፣ በዚህ የተነሳም በልቶ ለማደር ሲቸገሩ እንደነበር ያመለክታል፡፡

እንደ ወጣት ታሬ ሁሉ በአካባቢው የጉልበት ሥራ እየሠራ የሚተዳደረው ወጣት ዳኘው ጥላሁን የሲሚንቶ ገበያ ሲቀዛቀዝ የዕለት ጉርስ የሚሆን ገቢ አጥቶ እንደነበር ነው የገለጸው።በዚህም ሲሚንቶ ከመጫንና ከማውረድ ውጭ የሆኑ ማንኛውንም የጉልበት ሥራ በአካባቢው ሲሰራ መቆየቱን አመልክቶ፣ አሁን ግን የሲሚንቶ መሸጫ ሱቆቹ እየተከፈቱ መሆናቸውን ተናግሯል፤ ይህም የመጫንና የማውረድ ሥራውን እንዲቀጥል እንዳስቻለው ተናግሯል፡፡

ከሲሚንቶ አቅርቦት እጥረት ጋር በተያያዘ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴርን ሀሳብ ለማካተት ብንሞክረም አልተሳካልንም፤ ሚኒስቴሩ በጉዳዩ ላይ በቅርቡ በአምራቾቹ በኩል መግለጫ እንደሚሰጥበት በመግለጽ ምላሹን በዚያው ማግኘት እንደሚቻል አስታውቆናል።

አዲሱ መመሪያ ከወጣበት እስከ አለፈው ታኅሣሥ አጋማሽ ድረስ ለአምስት ወራት በሥራ ላይ በቆየው አሰራር መሰረት፤ የሲሚንቶ አከፋፋዮች የሚመረጡት በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች አማካኝነት ነበር። ባለፈው ታኅሣሥ አጋማሽ ይፋ የተደረገው አዲስ መመሪያ በአንጻሩ፤ ፋብሪካዎች “የሲሚንቶ ምርቱን ተደራሽ ያደርጉልኛል” የሚሏቸውን አከፋፋዮች ራሳቸው እንዲመርጡ ነጻነት የሰጠ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በወቅቱ በሰጠው መግለጫ አስታውቋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንደገለጸው፤ ከሐምሌ ወር ጀምሮ በመመሪያ የተተገበረው አሰራር ውጤቶችን ቢያስገኝም እንደ ምርት እጥረት ያሉ ተግዳሮቶች ግን ተፈጥረዋል። በአገሪቱ ከሚገኙና ከአስር የሚልቁ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ውስጥ በአግባቡ አምርተው ለገበያ ማቅረብ የቻሉት ከሶስት የሚበልጡ አልነበሩም።ሚኒስቴሩ ባለፈው ወር የሲሚንቶ ገበያ በነጻ ገበያ እንዲመራ ያሳለፈውን ውሳኔ ተከትሎ በገበያው ላይ የተወሰኑ ለውጦች እየታየ ስለመሆኑ የዝግጅት ክፍላችን በሰራው ዘገባ አመልክቶም ነበር።



የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያው በግብይት ላይ ለውጥ እያመጣ ቢሆንም፣ የአቅርቦት ችግር እንዳለ እየተጠቀመ ነው፤

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የባህል አብዮት በሂደት ወይስ በኃይል?

**ዋስልኝ አየለ**

የጥር ወር ብዙ የአገራችንን ባህሎች የምናይበት ነው።ባለፈው ሳምንት የከተራ፣ ጥምቀት እና ቃና ዘገሊላ በዓላትን አክብረናል።እነዚህ በዓላት ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን ባህላዊ ይዘትም እንዳላቸው ብዙ ተብሎለታል።ስለዚህ የጥር ወር የባህል ዓውደ ርዕይ ነው ማለት ይቻላል።

ሌላው የዚሁ የጥር ወር መገለጫ ደግሞ ሰርግ ነው።የከተማ ሰርግ ዘመናዊ መልክ ቢኖረውም በገጠሩ ማህበረሰብ ዘንድ ግን ቱባ ባህላዊ ይዘቱ ይታያል።

የጥምቀት ዕለት የአገራችንን የቴሌቪዥን ቻናሎች እያቀያየርኩ ሳይ ነበር የዋልኩ።በእንዲህ አይነት አጋጣሚዎች የቴሌቪዥን ጣቢያዎችን ማየት ሙሉ ኢትዮጵያን እንደማየት ማለት ነው።የሚዲያ ሚና ማለትስ ይህ አይደል?

ታዲያ እነዚህን የአገራችንን ውብ እና ድንቅ ባህሎች ሳይ (አብዛኞቹ ቀደም ብየም የማውቃቸው ቢሆኑም) ትዝ ያለኝ ከቀናት በፊት አጀንዳ ሆነው የነበሩ ሁለት ጉዳዮች ናቸው።አንደኛው፤ የምሥራቅ ጎጃም ዞን ያወጣው ቁምጣ ሱሪ መልበስን የሚከለክል ትዕዛዝ ነው።በእርግጥ ባጋጠመው ተቃውሞ መግለጫውን አንስቶታል።ሁለተኛው ደግሞ የሴት ሽማግሌዎች የላከው ዘማሪ ጉዳይ ነው።

ሁለቱንም አጋጣሚዎች ለመነሻ ሀሳብ ተጠቀምኳቸው እንጂ ስለእነርሱ ለማውራት አይደለም፤ ዳሩ ግን መነሻ ሀሳብ ይሆናሉና እግረ መንገድ ስለባህል አብዮት እናውራ።

ከምሥራቅ ጎጃሙ የቁምጣ ክልከላ እንጀምር!

የባህል አብዮት እንደሚያስፈልግ አምናለሁ።ድሮ እንዲህ ነበርንና አሁንም በዚያው እንቀጥል አይባልም።ምክንያቱም አሁን ያለው ሁኔታ የድሮውን አኗኗር ለመኖር አይፈቅድም።የዘመኑ ባህሪ እና ነባራዊ ሁኔታ ያስገድዳል።ለምሳሌ፤ የድሮ ባህላችን አገር አቋራጭ ጉዞ በእግር መሄድ ነበርና አሁንም እንሂድ አይባልም፤ ምክንያቱም የዛሬው ትውልድ እንኳን አገር አቋራጭ ጉዞ 10 ኪሎ ሜትር እንኳን መሄድ የሚከብደው ነው።

በአጠቃላይ የባህል አብዮት ይኖራል፤ ዳሩ ግን የባህል አብዮት የሚመጣው በሂደት እንጂ በትዕዛዝ አይደለም።ለምሳሌ፤ ቁምጣ ሱሪ በብዙ የገጠር አካባቢዎች እየቀረ ነው፤ የቀረው ግን በትዕዛዝ ሳይሆን በሰዎች ፍላጎትና አመለካከት መቀየር ነው።የሥራ ዘርፍ እና የአኗኗር ዘይቤ ሲቀይሩ ነው።

ሌላው ነባራዊ ሁኔታ ደግሞ ለሥራ የሚያመች ምርጫን ያላገናዘበ መሆኑ ነው።ገበሬው ቁምጣን የሚፈልገው ለቅልጥፍና ነው።ረጅም ሱሪ አድርጎ በጭቃ እየጎተተ እርሻ ማረስ አይመችውም።ይህን የሚያደርገው ሱሪ መግዣ ተቸግሮ ወይም ኋላቀር ሆኖ አይደለም፤ ለቅልጥፍና የሚመቸው ቁምጣ ስለሆነ ነው።ይህ ደግሞ ገበሬው ብቻ ሳይሆን ማንም የተማረ እና የሰለጠነ የሚባል ሁሉ የሚያደርገው ነው።ኳስ ጨዋታ ላይ ቁምጣ የሚለበሰው ለዝነጣ ተብሎ አይደለም፤ ቀለል እና ቀልጠፍ ያለ ስለሆነ ነው።የውሃ ዋና እና ሌሎች የስፖርት ዓይነቶች ቀለል ባለ አለባበስ የሚደረጉት የሥራው ባህሪ ስለሆነ ነው።የጋራዥ ሰራተኛ ሙሉ ቱታ የሚለብስ የሥራው ባህሪ ያንን ለመልበስ ስለሚያስገድድ ነው።ብዙ የሥራ ዘርፎች የየራሳቸው መለያ ልብስ አላቸው።ስለዚህ የባህል ለውጥ እናምጣ ሲባል ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

በዚሁ እግረ መንገድ ግን አንድ ትዝብት ላስቀምጥ።በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ተቋማት(በተለይም የዞን እና ወረዳ) የማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ ለትዝብት የሚዳርጉ ነገሮች እየታዩባቸው ነው።የወረዳ ገፆች የማህበራዊ ሚዲያ መሳቂያ እየሆኑ ነው።ስለዚህ ጠበቅ ያለ የግንዛቤ ማስጨበጫ ያስፈልጋቸዋል።ምክንያቱም በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ስለሆነ እንደ ተራ ግለሰብ ተንቆ የሚታለፉ አይደሉም፤ ኃላፊነት አለባቸው።ዝም ብሎ ድንገት ትዝ ያላቸውን ነገር በስሜት ሊለጥፉ አይገባም።

ሁለተኛው ትዝብቴ የሴት ሽማግሌዎች ነገር ነው።ዓለም አቀፉን መገናኛ ብዙኃን ቢቢሲ አማርኛ ጨምሮ ብዙ አካላት ነገሩን በስህተት የተረዱት ይመስለኛል።ቢቢሲ ‹‹የሴት ሽማግሌ›› መባሉን ያልተለመደ እና አዲስ ፈጠራ አስመስሎ ነው ያቀረበው።ከትርጓሜው እንነሳ።

‹‹ሽማግሌ›› የሚለው ቃል በእማሬያዊ ትርጉሙ በዕድሜ የገፋ ወንድ ማለት ነው።ዳሩ ግን በሂደት በማህበረሰቡ ተደራቢ ትርጉም ተሰጥቶታል።ሽማግሌ ማለት አስታራቂ፣ ሚዛናዊ፣ አዋቂ፣ ብልህ፣ በሳል አስተሳሰብ ያለው... ማለት ነው።በዋናነት ደግሞ አስታራቂ በሚለው ይታወቃል።

ከእነዚህ ትርጓሜዎች በመነሳት ባደኩበት ማህበረሰብ ውስጥ በዓይኔ ያየሁትን እና በጆሮዬ የሰማሁትን ባህል ልናገር።

እናቴ ‹‹ሽማግሌ ሆኜ›› ስትል ሰምቻት አውቃለሁ።ይህን የምትለው የተጣሉ የአካባቢ ሰዎችን ለማስታረቅ ስትሄድ ነው።ብዙ ሴት አስታራቂዎችን በአካባቢያችን አይቻለሁ።ለማስታረቅ ሲያስቡ ‹‹እናሽማግላቸው›› ነው የሚሉት።እንዲያውም ወንዶች ሳይሰሙ ተብሎ (ወደ ጠብ ስለሚወስዱት) በሴቶች ብቻ የሚያልቅ የእርቅ ሽምግልና አለ፡፡

በሌላ በኩል ሽምግልና የዕድሜ ጉዳይም አይደለም።ታላቅ ወንድማችን የ60 እና 70 ዓመት አዛውንቶች በአካባቢ እያሉ ገና በ30 ዓመቱ ሽምግልና ይቆጠር ነበር።መስፈርቱ ፆታ እና ዕድሜ አይደለም ለማለት ነው።ማን መናገር ይችላል፣ ማን ማሳመን ይችላል የሚለው ነው መስፈርቱ።አሸማጋይ የሚለውን ቃል negotiator የሚለው የእንግሊዘኛ ቃል ነው የሚተካው እንጂ Old የሚለው አይሆንም።

ብዙ ሰዎች በነገሩ ሲገረሙ የነበረው ሴት ሆነው እንዴት ሽማግሌ ይባላሉ በሚለው ነው።‹‹ልጅህን ለልጄ›› በሚለው ባህል ውስጥ የሴት ሽማግሌ መላክ አግባብ ነው አግባብ አይደለም የሚለውን ለጊዜው መወሰን ባይቻልም ሽማግሌ የሚለው ቃል ግን ለሂደቱ እንጂ ለፆታና ዕድሜ አይደለም።

ስለባህል አብዮት ስናወራ፤ ባህል በዘመን እና በሁኔታዎች መቀያየር የሚቀየር እንጂ ባለበት የሚቆይ አይደለም።የሰው ልጅ ከዛሬ አንድ ሺህ ዓመት በፊት የነበረበት ሁኔታ እና የዛሬው አንድ አይደለም፤ ከዛሬ አንድ መቶ እና አንድ ሺህ ዓመት በኋላም አሁን ባለበት አይገኝም።ምናልባትም ከዛሬ መቶ ምናምን ዓመታት በኋላ ቀሚስ የወንድ መገለጫ፣ ሱሪ ደግሞ የሴት መገለጫ ሊሆን ይችላል።ምክንያቱም ከዛሬ መቶ እና ሺህ ምናምን ዓመታት በፊት የነበሩትን ስንሰማ ‹‹ይደረግ ነበር እንዴ!›› ብለን ተገርመናል።

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን እና አፄ ዮሐንስ አራተኛን የምናውቃቸው በሹሩባ ነው።ይህ የሆነው ከ160 ምናምን ዓመታት በፊት ነው።ዛሬ ሹሩባ የሴት መገለጫ ነው።ሹሩባ የተሰራ ወንድ ሲታይ ‹‹ሴታሴት!›› እየተባለ ይሰደባል።ማን ያውቃል ከ200 ምናምን ዓመታት በፊት ሹሩባ የወንድነት መገለጫ የነበረ ቢሆንስ? መሪዎቹ ታዋቂ ስለሆኑ ታሪካቸው ተቀምጦ እንጂ ተራ ወንዶች ሁሉ ሹሩባ ይሰሩ የነበረ ቢሆንስ?

በዚያ ዘመን ሹሩባ የወንድነት መገለጫ ይሁን አይሁን አናውቅም፤ ሀቁ ግን ባህል በዘመን ሂደት ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ ገጽታ ሊይዝ ሁሉ ይችላል።ይህ የሰው ልጅ ዝግመተ ለውጣዊ ሂደት ነው።እንኳን ውጫዊ የሆነውን ባህል፣ ሥጋዊ የሆነው የሰውነት ቅርጽ እንኳን በሂደት ነው አሁን ያለውን ገፅታ የያዘው፡፡

ስለዚህ ባህል የሚለወጠው በሂደት እንጂ በኃይል ስላልሆነ የሰዎችን ባህል መከልከል ወይም መቃወም አግባብ አይደለም።

# ዓለም አቀፍ



## ቱርክ የስዊድንን የኔቶ አባልነት ማመልከቻ እንደማትደግፍ ተናገረች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የቱርክ ፕሬዚዳንት ጠይብ ረስፐ ኤርዶጋን በስቶክሆልም ቁርአን የተቃጠለበትን ተቃውሞ ተከትሎ የስዊድንን የኔቶ አባልነት ጥያቄ አንካራ እንደማትደግፍ አስታወቁ፡፡

በሳምንቱ መጨረሻ በስቶክሆልም በተደረጉ “ፀረ-እስልምና” ተቃውሞዎች ውጥረትን ተከትሎ የስዊድን የኔቶ አባልነት ጥያቄ ቱርክ አትደግፍም፡፡

በጋዜጣዊ መግለጫው ላይ ስዊድን ለቱርክ ወይም ለሙስሊሞች አክብሮት ካላሳየች “በኔቶ ጉዳይ ላይ ከእኛ ምንም አይነት ድጋፍ አታገኝም” ሲሉ ፕሬዚዳንቱ ገልፀዋል።

በስዊድን ዋና ከተማ ቱርክን በመቃወም እና ኩርዶችን በመደገፍ የተካሄደውን ተቃውሞ ተከትሎ ራስሙስ ፓሉዳን የተባሉ የዴንማርክ ቀኝ-አክራሪ ፖለቲከኛ በቱርክ ኤምባሲ አቅራቢያ ቁርአን አቃጥለዋል።

ኤርዶጋን ሰኞ እለት ቃጠሎው በተለይ ለሙስሊሞች “ስድብ” ነው ያሉ ሲሆን፤ ስዊድን ኩርድ ደጋፊ ሰልፎችን መፍቀዷን ተችተው፤ ስዊድን ሰልፉን መፍቀድ የሚያስከትለውን ውጤት ማስላት ነበረባት ሲሉም አክለዋል።

ቱርክ ስዊድን ኔቶን እንድትቀላቀል ያቀረበችውን ተቃውሞ ለመቅረፍ የስዊድን የመከላከያ አዛዥ ወደ አንካራ ሊያደርጉት የነበረውን ጉብኝትንም ሰርዛለች።

አንካራ ቀደም ሲል ስዊድን እና ፊንላንድ 130 የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን አሳልፈው እንዲሰጡ አስቀድማ በመጠየቅ የአባልነት ማመልከቻ ድጋፍ ለመስጠት እግሯን ጎትታ እንደነበር የተነገረ ሲሆን ስዊድን ግን ሁኔታው ግዙፍ እንዳልሆነ ተናግራለች።

የሀገሪቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቶቢያ ቢልስትሮም እንደተናገሩት ማመልከቻው ወደ እልባት ተቃርቧል ብለዋል።

## የአገሪቱ የወሊድ መጠን መቀነስ እንዳሳሰባት ጃፓን ገለጸች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

<u>አዲስ አበባ፣</u> በጃፓን ያለው የወሊድ መጠን መቀነስ አሳሳቢ መሆኑ የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ፉሚዮ ኪሺዳ መግለጻቸዉን ቢቢሲ ዘገበ።

የጃፓንን ጎረቤቶች ጨምሮ በብዙ አገራት የወሊድ መጠን እየቀነሰ ሲሆን በጃፓን በሕይወት የመቆየት መጠን እየጨመረ ሲመጣ የወሊድ መጠን መቀነሱ ተገልጿል፡፡ በዚህ ምክንያትም የአረጋውያን ቁጥር እየጨመረ የወጣቶች ቁጥር እየቀነሰ መጥቷል።



ጃፓን በዓለም ከ65 ዓመት በላይ በሆኑ ሰዎች ብዛት ሁለተኛ ደረጃ ላይ ስትሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩ “እንደ ማኅበረሰብ እንቀጥላለን ወይ የሚለው አጠያያቂ ደረጃ ደርሷል። ልጆች ተኮር ፖሊሲዎች ትኩረት ይሻሉ። በዚህ ዘርፍ የሚሠራው ሥራ አሁን ካለው እጥፍ ወጪ ያስፈልገዋል። ግንቦት ላይ ይህን ጉዳይ የተመለከተ ዘርፍ ይቋቋማል” ሲሉ ለአገሪቱ ሕግ አውጭዎች ተናግረዋል።

የጃፓን የሕዝብ ቁጥር በአውሮፓውያኑ 2017 ከነበረበት 128 ሚሊዮን በምዕተ ዓመቱ መጨረሻ ወደ 53 ሚሊዮን እንደሚወርድ በ2020 የወጣ ጥናት ይጠቁማል።

ጃፓን ስደተኞች የምትቀበልበት ሕግ ጥብቅ ቢሆንም በቅርቡ በመጠኑ የላላ ሲሆን በኑሮ ውድነት፣ በሥራ እና በኑሮ የሚጠመዱ ሴቶች ቁጥር መጨመር፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ ተደራሽነት መስፋት እና ሴቶች ውስን ልጆች ብቻ ለመውለድ መወሰናቸው ለወሊድ መጠን መቀነስ አስተዋጽኦ ማድረጉ ተነግሯል፡፡


በ2050 ከጃፓን ሕዝብ አንድ ሦስተኛው እንደማይኖር የተገመተ ሲሆን በአገሪቱ ከውጭ ዜጎች የተወለዱ 3 በመቶ ብቻ መሆናቸዉም ተገልጿል፡፡

የኑሮ ውድነት መባባስ ለወሊድ መጠን መቀነስ አንዱ ምክንያት ሲሆን፣ ጃፓን የሠራተኞች ክፍያን ባለፉት 30 ዓመታት እንዳላሻሻለችና ስደተኞችን መግፋት ዋጋ የሚያስከፍላቸው አገራት ምሳሌ እንደምትሆንም ተጠቅሷል፡፡

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# አምሀ እሸቴ - የኢትዮጵያ ሙዚቃ ባለውለታ



ማህሌት አብዱል

የሙዚቃ ታሪክ ሲወሳ ከፍተኛውን ድርሻ ይዘው ታሪካቸው የሚነገርላቸው፤ ህዝብም የሚያውቃቸው ድምፃውያኑ ብቻ ናቸው። ከድምፃውያኑ ጀርባ ሆነው ሙዚቃውን ሙዚቃ ያደረጉ ባለሙያዎች ባስ ሲልም ከነጭራሽ ስማቸውን የሚያነሳ የለም። አልያም በሥራቸው ልክ ታሪካቸው አልተነገረላቸውም። በተመሳሳይ ሙዚቃው ተከሽኖ አድማጭ ዘንድ እንዲደርስ ድልድይ የሚሆኑት አቀናባሪዎች (ፕሮዲውሰሮች) ታሪክ ከነጭራሹ አስታዋሽ ሳያገኝ ነው የቆየው። ይህንን ድልድይ ከገነቡና የኢትዮጵያን የዘመናዊ ሙዚቃ ቅጂ ኢንዱስትሪ ሕይወት ከዘሩበት ሰዎች አንዱና የዘርፉ ፊር ቀዳጅ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የቅጂ (ሪከርዲንግ) ባለቤት አምሃ እሸቴ ናቸው።


በ1950ዎቹ አዲስ አበባ ከምዕራባውያኑ የዘመናዊ ሙዚቃ ስልት ብሉስ፣ ሶልና ሮክ ኤንድ ሮል ጋር የተዋወቀችበት ዘመን ነበር። በተለይም የዚህ ዘመን ወጣቶች ለእነዚህ የውጭ ሙዚቃዎች የተለየ ፍቅር እያሳደሩ ቢሄኑም እንደልባቸው ሙዚቃውን አግኝተው የሚያዳምጡበት እድል ግን አልነበራቸውም። ታዲያ የዚያን ዘመን ወጣቶች ለእነዚህ የሙዚቃ ስልቶች ያላቸውን ጥማት የሚያስታግሱበት የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮን በማድመጥ ብቻ ነበር።

አምሃ እሸቴም በወጣትነት እድሜያቸው የእነዚህ የዘመኑ ተወዳጅ የሙዚቃ ስልቶች አፍቃሪ ነበሩ። ይሁንና በነበረው የአቅርቦት ችግር ምክንያት እሳቸውም ሆኑ ጓደኞቻቸው እንደልባቸው ሙዚቃዎቹን አግኝተው መዝናናት አልቻሉም። አምሃ ይህንን ችግር ለመፍታት የራሳቸውን ሙዚቃ መደብር ለመክፈት ይወስናሉ። በዚህ ጊዜ አምሃ ለስራ ጉዳይ አስመራ የሚሄዱበት አጋጣሚ ይፈጠራል። በጊዜው አሜሪካ ቃኘው የተሰኘ የጦር ሰፈር በአስመራ ነበራት። ይህ የአሜሪካ ጦር ሰፈር ወታደሮቹ የሚዝናኑበት የራሱ ሬዲዮ ጣቢያ ነበረው። አምሃ አስመራ በቆዩባቸው ጊዜያት አዲስ አበባ እያሉ ይጓጓላቸው የነበሩ ሙዚቃዎች በቃኘው ሬዲዮ እንደልባቸው የመኮምከም እድል አገኙ። ስለዚህ አጋጣሚ አምሃ ሲናገሩ ‹‹በጊዜው በሙዚቃው ተመስጬ ለሰዓታት ከተቀመጥኩበት አልነሳም ነበር›› ይላሉ።

በአስመራ አሜሪካኖቹ ከፍተውት የነበረው የቃኘው ኤፍ ኤም ሬዲዮ ጣቢያ የሙዚቃ ፍቅራቸውን በእጥፍ እንደጨመረላቸው ይናገራሉ። በአዲስ አበባም ቢሆን የክቡር ዘበኛ ንብረት የነበረው የጠቅል ሬዲዮ ጣቢያ አልፎ አልፎ የሚለቃቸውን ሙዚቃዎች መስማት የመንፈስ ሀሴትን ያጎናፅፋቸው ነበር።

### ጅማሮ "ሃራምቤ" የሙዚቃ መደብር

አምሃ በጊዜው የውጭ የሙዚቃ ሪኮርዶችን ከአሜሪካ ለማስመጣት ብዙ ፈተናዎች ነበሩባቸው። በመጀመሪያ ደረጃ በቂ ገንዘብ እጃቸው ላይ አልነበረም፤ ሁለተኛ ሪከርዶቹ ቢመጡም ሱቅ የሚከፍቱበት ቦታ ገና አላዘጋጁም። ሆኖም ገንዘቡ በብድር ሲገኝ የቦታው ጉዳይ አራዳ ከአንድ ልብስ ሰፊ ዘንድ ጥገኝነት በማግኘት ተፈታ። አምሃ ከውጭ ያዘዟቸውን ሙዚቃዎች አዲስ አበባ ሲደርሱ የመጀመሪያዋ ‹‹ሃራምቤ›› ሙዚቃ ቤት ተከፈተች። የነጀምስ ብራውን፣ ጂም ሬቭስ፣ ኦቲስ ሬዲንግ እና ዊልሰን ፒኬትን ሙዚቃዎች የያዘችው ሃራምቤ ገና በተከፈተች እለት ነበር ገበያዋ የደራው። ገና በመጀመሪያው ቀን ከመጡት ሪከርዶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተሸጠው አለቁ። በገበያው ሁኔታ ሞራላቸው የተነሳሳው አምሃ ሌሎች ተጨማሪ ሪኮርዶችን አዘው ንግዱን ማጧጧፍ ተያያዙት። የአዲስ አበባ ወጣትም የልቡ ደረሰ። ሃራምቤ ቁጥር ሁለት በፒያሳ ስትከፈት ከአዲስ አበባ ውጪም በናዝሬት፣ በአስመራና በድሬዳዋ አምሃ ሙዚቃ ቤቶችን መክፈት ቻሉ።



**ደርግ ወደ ስልጣን በመጣበት ዓመት የጥላሁን ገሠሠን፤ የአለማየሁ እሸቴን፤ የተክሌ ተስፋእግዚን፤ እና የሙሉቀን መለሰን ስራ ለመስራት ወደ ግሪክ ተጉዘው ነበር። ስራዎቹ ካለቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲላኩ የተክሌ ተስፋእዝጊ ትግርኛ ሙዚቃ ጉምሩክ ላይ እንዳይገባ ታገደ። ምክንያቱ ደግሞ ስርዓቱን የሚቃወም ነው በሚል ነበር**

### ከሙዚቃ መደብር ወደ ሙዚቃ ሪኮርድ

ካሰቡት በላይ ገበያው የቀናቸው አምሃ ከአሜሪካ በተጨማሪ ከኬኒያ፣ ከሱዳን፣ ከህንድ እና ከምዕራብ አፍሪካ ሃገራት ሙዚቃዎችን ማስመጣት ቀጠሉ። በተለይም ከሱዳን የመሃመድ ወርዲ ሙዚቃዎች እጅግ ተወዳጅ ነበሩ። አንድ ጥያቄ ግን አምሃ ጭንቅላት ውስጥ ይመላለስ ነበር። ይኸውም ‹‹የኢትዮጵያ ሙዚቃስ? የሚል ነበር።

አምሃ የውጭ ሃገር ሙዚቃዎችን እያስመጡ ከመሸጥ በተጨማሪ በሃገር ውስጥ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞችን ስራ ፕሮዲውስ ማድረግ አለብኝ ብለው ማሰብ ጀመሩ። ይህ ግን ቀላል አልነበረም። ከባድ ያደረገው ደግሞ የገንዘብ ችግር ሳይሆን የህግ ጉዳይ ነው። በወቅቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሙዚቃ የማሳተምና የማከፋፈል ስራ የባለቤትነት መብት በህግ የተሰጠው የሃገር ፍቅር ቲያትር ቤት ብቻ ነበር። ይህ የሞኖፖል መብት በህግ ለቲያትር ቤቱ ቢሰጠውም ቲያትር ቤቱ ግን ለ20 ዓመታት ያህል ምንምአይነት ሙዚቃ አላሳተመም ነበር።

ይህን የተመለከቱት ወጣቱ አምሃ ‹‹ለምን እኔ አላሳትምም?›› ሲሉ በድፍረት ተነሱ። በወቅቱ ከትያትር ቤቶቹ የተሰጠው ምላሽ ‹‹መብቱ የኛ ነውና እንዳትሞክረው›› የሚል ዝግ መልስ ነበር። አምሃ ጉዳዩ አስጨነቃቸው። የንጉሰ ነገስቱን ህግ መጣስ ደሞ የሚያመጣውን መዘዝ ያውቃሉ። በሌላ ጎኑ እሳቸው የተለያዩ የውጭ ሀገራትን ሙዚቃ እያመጡ እየሸጡ የሀገራቸው ሙዚቀኞች በሸክላ አለመቀረፅ፣ ለሌላውም ዓለም አለመተዋወቅ ከንክኗቸዋል።

ያለው አማራጭ በድፍረት አሳትሞ የሚመጣውን በፀጋ መቀበል ብቻ ሆነ። ለዚህ ደግሞ የሚተባበር ድምፃዊ ያስፈልጋል። አምሃ የሚያውቃቸውን ዘፋኞች አማከሩ። ሁሉም ፈሩ። ‹‹አዬ ጦስ ታመጣብናለህ›› እያሉ ወደኋላ አፈገፈጉ። በዚህ መሀል አንድ ወጣት ድምፃዊ ብቅ አለ። ድምፃዊው ከአምሃ ጋር የማይደፈረውን ለመድፈር ተስማማ። ‹‹ከታሰርንም እየዘፈንን አብረን እንገባለን›› ሲል የአምሃን ልብ በወኔ ሞላው። እናም ሆነ። እንደተፈራው እዚህ ግባ የሚባል ቅጣት ግን አልነበረም።

ይህ ድምፃዊ ተወዳጁ አለማየሁ እሸቴ ሲሆን በአጋጣሚውም በአምሀ እሸቴ ሪከርድስ አማካኝነት የመጀመርያ የሸክላ ሙዚቃ አሳታሚ ለመሆን በቃ። ይህም ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ በጀርመን ሀገር ካሳተሙት መዲናና ዘለሰኛ፣ ከነፈረደ ጎላ የሸክላ ስራ፣ እንዲሁም በጣሊያን ወረራ ወቅት ከታተሙ ጥቂት ሸክላዎች በኋላ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ውስጥ ፊር ቀዳጅ ህትመት ለመሆን በቃ።

በዚህ መሰረት በአምሃ ሪከርድስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሙዚቃው የታተመለት አለማየሁ እሸቴ ነበር። ስራዎቹ ደግሞ ‹‹ትማርኪኛለሽ›› የተሰኘ የአማርኛ ዘፈንና አንድ የሱዳንኛ ዘፈን ነበር። እነኚህ ዘፈኖች በ1961 ዓ.ም ህንድ ሃገር ተሰርተው በሃራምቤ ሙዚቃ ቤት ለገበያ ሲቀርቡ ተቀባይነታቸው ከፍተኛ ሆነ። ቀጠለናም ሌላ የአለማየሁ እሸቴ ነጠላ ዜማ ታተመ። ከዚያ በኋላማ አምሃ ሪከርድስ በኢትዮጵያ ሙዚቃ ፕሮዳክሽን ነገሰበት።

ሙላቱ አስታጥቄ፣ ግርማ በየነ፣ ጌታቸው ካሳ፣ ተስፋማርያም ኪዳኔ፣ ተሾመ ምትኩ፣ ሰይፉ ዮሐንስ የመሳሰሉት እውቅ የሙዚቃ ስራዎች በአምሃ ሪከርድስ ታትመው ለገበያ ቀረቡ። ከእነዚህ መካከል የካሳ ተሰማ ‹‹ትዝታ›› የተሰኘው ሙዚቃ አምስት ሺ ኮፒ በመሸጥ ክብረወሰኑን ሰበረ። የአምሃ ሪከርድስ ስኬት ሌሎች ሰዎችን ወደእዚህ ኢንዱስትሪ እንዲቀላቀሉ መንገድ የጠረገ ሆነ። ካሳሁን እሸቴ (ፊሊፕስ) እና አሊታጎ (ካፊያ ሪኮርድስ) አምሃ በቀደደው መንገድ የመጡ ናቸው።

አምሃ ለሙዚቀኞች ይከፈል የነበረውንም አነስተኛ ክፍያ እንዲለወጥ የበኩላቸውን ጥረት ያደረጉ ሰው ነበሩ። በ1966 ዓ.ም ገደማ ለመሃሙድ አህመድ ለአንድ ነጠላ ዜማ ሁለት ሺ ብር በመክፈልም መሃሙድን የጊዜው ከፍተኛ ተከፋይ አድርገውት ነበር። በዚህ ጊዜ የአብዛኞቹ ስመ-ጥር ዘፋኞች ወርሃዊ ደመወዝ በአማካይ ከ200 ብር እንደማይበልጥ ሲታወስ ለነጠላ ዜማው የተከፈለው ገንዘብ ምን ያህል ከፍ ያለ እንደሆነ ለመገመት አያዳግትም።

### ሶል ኤኮስ ባንድ

አምሃ ከፕሮዳክሽን ስራው ባሻገር ስኬታማ የሆነ የሙዚቃ ባንድ ማቋቋም ችለው ነበር። ሶል ኤኮስ የተባለው ይኸው ባንድ በድምፃዊነት አለማየሁ እሸቴንና ተሾመ ምትኩን ያቀፈ ሲሆን አሉላ ዮሐንስ ሊድ ጊታር፤ ታምራት ፈረንጅ ትራምፔት፤ መሰለ ገሰሰ ድራም፤ ተኪ አድሃኖም ጊታር፤ እንዲሁም ቴዎድሮስ ምትኩ ሳክስፎን ይጫወቱ ነበር። በሶል ኤኮስ ባንድ ተሰርተው ተወዳጅነት ካተረፉ ሙዚቃዎች መካከል የተሾመ ምትኩ ‹‹ጋራ ስር ነው ቤትሽ›› እንዲሁም የሰይፉ ዮሐንስ ‹‹ኤቦ ላላ›› ተጠቃሽ ናቸው።

ሶል ኤኮስ ባንድ በዘመኑ በሂልተን ሆቴል ምርቃት እንዲጫወት የተመረጠ ባንድ ከመሆኑም ባሻገር በአዲስ አበባ ትልልቅ የሰርግ ፕሮግራሞች ላይ የሚፈለግ ባንድ ነበር። ከአዲስ አበባ ውጭም በክፍለሃገር ከተሞች እየተጋበዘ የተጫወተ ስመጥር ባንድ ነበር።

### የአምሃ የስደት ህይወት

‹‹ደርግ ወደ ስልጣን ሲመጣ ነጻነታችንን ይዞ የመጣ መስሎን እጃችንን ዘርግተን ነው የተቀበልነው›› ይላሉ አምሃ። ዳሩ ግን ነገሮች ሁሉ እንደታሰበው አለመሄዳቸውን ይገልፃሉ። ደርግ ወደ ስልጣን በመጣበት ዓመት የጥላሁን ገሠሠን፤ የአለማየሁ እሸቴን፤ የተክሌ ተስፋእግዚን፤ እና የሙሉቀን መለሰን ስራ ለመስራት ወደ ግሪክ ተጉዘው ነበር። ስራዎቹ ካለቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ሲላኩ የተክሌ ተስፋእዝጊ ትግርኛ ሙዚቃ ጉምሩክ ላይ እንዳይገባ ታገደ። ምክንያቱ ደግሞ ስርዓቱን የሚቃወም ነው በሚል ነበር። ዘፈኑ ከመከልከሉም በተጨማሪ በዘፈኑ ስራ የተሳተፉ ባለሙያዎችና የአምሃ ወላጅ አባት ታሰሩ። ይህንን የሰሙት አምሃ ለራሳቸው ደህንነት ስለሰጉ በወጡበት ቀሩ።

በስደት በኖሩበት አሜሪካም አምሃ ከሙዚቃው ዘርፍ አልተለዩም ነበር። በዋሽንግተን ዲሲ ቡሉናይል የተሰኘ ክለብ በመክፈት በከተማው አንዱ ተወዳጅ ክለብ እስከመሆን ደርሶም ነበር። ከአገር ቤት እነ ግርማ በየነን፤ መሃሙድ አህመድን፤ ጌታቸው ካሳን የመሳሰሉ ድምፃውያንን ያቀፈ ቡድን በማስመጣትም በአሜሪካ በትልልቅ መድረኮች ላይ ስራዎቻቸውን እንዲያቀርቡ ረድተዋቸዋል። ምስጋና ለፍራንሲስ ፋልሴቶ አምሃ እጅ የነበሩ ኦርጅናል ሪኮርዶች በኢትዮጲክስ ስብስብ ውስጥ መካተት ችለዋል። አምሃም ይህንን የፋልሴቶን ጥረትና ስራ እጅግ አድርገው ያመሰግኑም ነበር።

### የአምሃ ሌጋሲ

አምስት አስርት ዓመታትን ባስቆጠረ ጉዞ አምሃ ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ኢንዱስትሪ አይተኬ ሚናን ተጫውቷል። የሙዚቃ መደብር በመክፈት፤ የኢትዮጵያ ሙዚቀኞችን ስራ ፕሮዲውስ በማድረግ፤ በማሳተም፤ በማከፋፈል እንዲሁም በማማከር ረገድ የዋሉት ውለታ ታሪክ ሊዘነጋው የሚችል አይደለም። ብዙ ስራዎችን የሰራው ግርማ በየነ በአንድ ወቅት ሲናገር አምሃ በስራው ልክ እውቅና አልተሰጠውም ብሏል። እውነት ነው፤ ለኢትዮጵያ የሙዚቃ ኢንዱስትሪ ላበረከተው አስተዋፅኦ በቅጡ አልዘከርናቸውም።

በሀገራችን በግለሰብ ደረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ የሸክላ ሕትመትን የጀመሩትንና ለሙዚቃችን ታላቅ አስተዋፅዖ ያደረጉትን አቶ አምሀ እሸቴ በህክምና ሲረዳ ቆይቶ ሚያዚያ 22 ቀን 2013 ዓ.ም በ74 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተውናል። በአገራችን የመንግስት የሙዚቃ ባንዶች ብቻ በነበሩበት እና ከአገር ፍቅር ማህበር ውጪ ሙዚቃን ማሳተም በማይፈቀድበት በግለሰብ ተነሳሽነት ሙዚቃን ለማሳተም የደፈሩ አቶ አምሀ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃን ካዘመኑት አሳታሚና አከፋፋዮች ግንባር ቀደሙን ሰው በዛሬው በባለውለታዎቻችን አምድ እንዲህ ልንዘክራቸው ወደናል! ቸር እንሰንብት!።

# ስፖርት





## አትሌቲክሱን ለማገዝ ተስፋ የተጣለበት የአየር ብክለት መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ

ዓለማየሁ ግዛው

የአካባቢ ተጽእኖዎች በስፖርት እንቅስቃሴዎች ላይ በተለያየ መንገድ አዎንታዊና አሉታዊ አሻራ ሊያሳርፉ እንደሚችሉ ሳይንሳዊ ግኝቶች በተደጋጋሚ አረጋግጠዋል። በተለይም ከአተነፋፈስ ስርአት ጋር በእጅጉ ቁርኝት ያላቸው እንደ አትሌቲክስ ያሉ ስፖርቶች በተበከለ አየርና ከፍተኛ ሙቀት የመታወክ እድላቸው ሰፊ በመሆኑ ልምምዶችና ውድድሮችን በተስማሚ የአየር ንብረት ማድረግ ግዴታ እየሆነ መጥቷል። ያደጉት አገራት ይህን በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ ምክንያት የሚመጣን ፈተና ለመወጣት ቴክኖሎጂዎችን እንደ አንድ አማራጭ መጠቀም ከጀመሩ ሰነባብተዋል። በኢትዮጵያም በተለይም አትሌቶችና አሰልጣኞች ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀሙ እድል ባይኖራቸውም ምቹ የሆነ የአየር ጸባይ ያለበትን አካባቢ እየፈለጉ ከከተማ ውጪ ልምምዶችን ሲሰሩ ማየት የተለመደ ነው።

የዓለም አትሌቲክስም በዚህ ረገድ 214 አባል ፌዴሬሽኖችን በአንድ አድርጎ ከ2020-2030 የሚተገበርና ቀጣይነት ያለዉ ስትራቴጂ በመቅረጽ የአየር ንብረት ለውጥ ስፖርቱ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ለመዋጋት እየሰራ ይገኛል። ዋና ዓላማውም በ2030 ከካርቦን ልቀት ነጻ የሆነ ተቋምን ለመገንባት ነው። የአስር ዓመቱ እቅድ የተዘጋጀው በአካባቢ፣ ማህበረሰብና ኢኮኖሚ ላይ ተጨባጭ ጥቅሞችን ለማድረስ ሲሆን በዚህም የስፖርትንና የአትሌቲክስን ጉልበት በመጠቀም ለማህበረሰብ የተሻለ ዓለምን ለመፍጠር ያለመ ነው። ስትራቴጂው ከፍተኛ ቁርጠኝነትና ቀጣይነት ያላቸው መርሆችና ተግባራዊነትን ያቀፈም ነው።

የአየር ንብረትና የአየር ብክለት ጉዳይ በአሁኑ ወቅት የተለያዩ የቤት ውስጥና የቤት ውጪ የስፖርት ውድድሮችን የማዘጋጀት ፍቃድ ለማግኘት እንደ ቁልፍ ጉዳይ እየታየ ይገኛል። ዓለማችን በአየር ንብረት ለውጥ ስጋት ውስጥ እየወደቀች በምትገኝበት በዚህ ወቅት በተለያየ መንገድ ወደ አካባቢ አየር የሚለቀቀው በካይ ጋዝ በስፖርት ውድድሮች ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ውጤታማነት ላይ እንቅፋት እየሆነ ይገኛል። እነዚህን በአየር ብክለት ምክንያት የሚመጡትን ተጽዕኖዎች በመቆጣጠር ለስፖርት ዝግጅቶች ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋልም ይህን ተጽእኖ ለማስቀረት እየተወሰደ የሚገኝ አንዱ ርምጃ ነው። ዘመን አመጣሽ ቴክኖሎጂዎችም የተበከለ አየርን በማጥራት፣ ከፍተኛ ሙቀትን በመቀነስና ቀዝቃዛውን ወደ ተስተካከለ አየር በመቀየር ለስፖርተኞች ምቹ ነገርን በመፍጠር ለውድድሮች መሳካት የጎላሚናን በመወጣት ላይ ይገኛሉ።



ቴክኖሎጂው ስፖርቱን ታሳቢ አድርጎ ይሰራ እንጂ ለከተማውም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተጠቁሟል፣

በኢትዮጵያ ለስፖርተኞች በተለይም ለአትሌቶች ምቹ የአየር ሁኔታን የመፍጠርና ከብክለት የጸዳ አካባቢን እውን የማድረግ ስራ ከአምስት ዓመት በፊት ተሞክሮ እንደነበር ይታወሳል። ጀግናው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት በነበረበት ወቅት የአየር ብክለት መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጂ በአዲስ አበባ ስቴዲየም ተገጥሞ የነበረ ቢሆንም ቴክኖሎጂው የፈጠረው ተፅእኖ፣ ያመጣው ለውጥና ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ይህ ነው ሳይባል ቆይቷል።

በቅርቡ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በተካሄደው የምስራቅ አፍሪካ ሪጅን አትሌቲክስ ምክር ቤት ጉባኤ የአየር ብክለት መቆጣጠርያ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ስራ የማስጀመር መርሃግብር ተከናውኖ ነበር። ቴክኖሎጂው በይፋ ስራ መጀመሩ በወቅቱ በነበረው መርሃግብር የተገለፀ ሲሆን፣ የስፖርቱን ማህበረሰብ በተለይም የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ለአካባቢ ቀጣይነት እየተጫወቱ ያሉትን ሚና የሚያሳይ እንደሚሆን ተጠቁሟል። የአየር ጥራት መቆጣጠሪያ መሳርያው በአካባቢ አየር ውስጥ የሚገኘዉን የተበከለ አየር (ካርቦን ዳይ ኦክሳይድ) በመሰብሰብ ስፖርተኞች ንጹ አየር በመተንፈስ ውጤታማ እንዲሆኑ አስተዋጾው ከፍተኛ እንደሚሆን ተገልጿል።

በወጣቶች ስፖርት አካዳሚ የተገጠመው የአየር ጥራት መቆጣጠርያ (air quality sensor) ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንና በኬንያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የጋራ ትብብር ሲሆን፣ የተከላው ስራ የተከናወነው በተባበሩት የአካባቢ ፕሮግራም አፍሪካ እና በስቶክሆልም ኢንስቲትዩት አፍሪካ ሽርክና መሆኑ ተገልጿል። ይህም በኢትዮጵያና በምስራቅ አፍሪካ አትሌቲክሱን የማገዝና የተሻለ የማድረግ አንድ እርምጃ እንደሆነ ታምኖበታል።

ቴክኖሎጂው ስፖርቱን ታሳቢ አድርጎ ይስራ እንጂ ለከተማውም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተጠቁሟል። ከቴክኖሎጂው ባሻገር ከሰው ሰራሽ የተፈጥሮ ጸጋዎችን መንከባከብም የአየር ብክለትን ለመቀነስ አንዱ መፍትሄ በመሆኑ የአትሌቲክሱና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን እንዲወጡ ጥሪ ቀርቧል። ለዚህም ምሳሌ እንዲሆን የዓለም ቻምፒዮኗ አትሌት ለተሰንበት ግደይና አትሌት ታደሰ ወርቁ ቴክኖሎጂው በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ሲገጠም ከተገኙት እንግዶች ጋር በጋራ በመሆን ችግኝ ተክለው የድርሻቸውን በመወጣት ፋና ወጊ ሆነዋል።

የአየር ጥራት መቆጣጠርያ (air quality sensor) መሳሪያ ስራውን በይፋ ያስጀመሩት የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽንና የምስራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ፌዴሬሽኖች ማህበር ፕሬዚዳንትና የስራ ኃላፊዎች በተገኙበት ሲሆን፣ የኢፌዴሪ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር፣ የጤና ሚኒስትር፣ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተወካዮች ተገኝተው ቴክኖሎጂው በይፋ ስራ መጀመሩን አብስረዋል።


## የጨረታ ማስታወቂያ

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ከ/ጠ/ዞን/የሙዱላ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት ለሙዱላ ማዘጋጃ ቤታዊ የሙዱላ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የኮብልስቶን መንገድ ግንባታና የዲች ግንባታ የጨረታ ማስታወቂያ መ/ቤታችን ከመንግሥትና ከህብረተሰብ ተሳትፎ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሙዱላ ከተማ የውስጥ ለውስጥ የዲች ግንባታ በማካሄድ የህብረተሰብ ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የልማት ሥራዎችን በመስራት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የዲች ግንባታና ኮብልስቶን ንጣፍ ሥራ ጠቅላላ ዋጋ በግልጽ በጨረታ አወዳድሮ ለማሠራት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሠረት:

ሀ. የዲች ግንባታ ሥራ

1. ከአቶ ገብርኤል ጡሜቦ እስከ ብርሃነሽ ሰዋሬ ሎት 1 የዲች ግንባታ 165 ሜ
2. ከአቶ አዳነ ሄጀቦ እስከ አየለ ሂራሞ ሎት 2 የዲች ግንባታ 200 ሜ
3. ከአቶ ሀይሌ ቃልቦሬ እስከ ታሪኩ ተክሌ ሎት 3 የዲች ግንባታ 126 ሜ
4. ከአቶ ሀ/ሚካኤል አኒቶ እስከ ኢዮብ ሄልሳቦ የሪቴይኒንግ ግንባታ 100 ሜ
5. ከአቶ ለማ ጡሜቦ እስከ ማትዎስ መናሞ የሪቴይኒንግ ግንባታ 115 ሜ

ለ. የኮብልስቶን ንጣፍ ስራ (የጨረታ ለመወዳደር መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች)

1. ከአቶ እርዳው ጆርጋ እስከ ቴሌ መጨረሻ ሎት የኮብልስቶን ንጣፍ ስራ 988 ሜ
2. ከአቶ ገብረ ሚካኤል ጡሜቦ እስከ ብርሃነሽ ሰዎረ ሎት 7 የኮብልስቶን ንጣፍ ስራ 1350 ሜ
3. ከአቶ አዳነ ሂጃቦ አስከ አበራ አጤቦ ሎት-8 የኮብልስቶን ንጣፍ ስራ 1760 ሜ
4. ከአቶ አበራ አጤቦ አስከ አቶ አየለ ሄራሞ ሎት -9 የኮብልስቶን ንጣፍ ስራ 1970 ሜ
5. ከአቶ ኃይሌ ቀልቦረ እስከ አቶ ታሪኩ ተክሌ ሎት -10 የኮብልስቶን ንጣፍ ስራ 1330 ሜ

- ለዲች ግንባታ GC ደረጃ 9 እና ከዚያ በላይ
- ለኮብልስቶን ሥራ የኮብልስቶን ጌጠኛ ድንጋይ ንጣፍ ፍቃድ ያለው
- ሁሉም በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ያለው
- የዘመኑን ግብር የከፈለ
- የንግድ መለያ ቁጥር /TIN NO/ ያላቸው
- የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቫት ተመዝጋቢ የሆነ
- ወቅታዊ የመልካም የሥራ ዋስትና ማቅረብ የሚችል
- የቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያለው/ያላት
- ሂሳብ ስህተት ከሁለት/2% በላይ ከሆነ ከጨረታው ይወገዳል
- ሳይት ምልክት ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡
- ከመሐንዲስ ግምት 15% ከፍ/ ዝቅ ያለው ተጫራች ከጨረታው ውድቅ ይሆናል፡፡
- ቅድሚያ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ትንታኔ ሳያደርግ ዋጋ ያቀረበ ተጫራች ውድቅ ይሆናል፡፡
- ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ሁለት ፐርሰንት (2%) በባንክ የተረጋገጠ CPO ከቫት በፊት ሞልተው ማቅረብ አለባቸው፡፡
- በየትኛውም ከተማ አስተዳደር በጨረታ አሸንፎ በሥራ ላይ ያለ ድርጅት ለመወዳደር ከከንቲባ ጽ/ቤት መጨረሱን የሚገልጽ የግምገማ ድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡
- አንድ ተጫራች ከአንድ ሎት በላይ መወዳደር አይችልም።
- ተጫራቾቹ የጨረታ ሰነድ ወይም ዋጋ የሞሉበትን ሰነድ ዋና እና ኮፒ የተሰራ ማስረጃ ዋና እና ኮፒ በተለያዩ በሰም አሸገው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ተጫራቾች በእያንዳንዱ የጨረታ ሰነድ ላይ ፊርማ እና የድርጅቱን ማህተም ማስቀመጥ ይጠበቅባቸዋል፡፡
- አሸናፊ የሆነው ድርጅት የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፈበት ጠቅላላ ዋጋ 10% በባንክ የተረጋገጠ ዋስትና ማቅረብ አለበት።
- በሳይት የተጀመረ ሥራ መጨረሱን የድጋፍ ደብዳቤ ከአደራጅ መስሪያ ቤት ማቅረብ የሚችል፡፡
- ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ትንታኔ ሳያደርጉ ዋጋ ያቀረቡ ተጫራቾች ውድቅ ይሆናሉ፡፡
- አሸናፊ የሆነው ድርጅት የጨረታ ማስከበሪያ ከአሸነፈበት ጠቅላላ ዋጋ ላይ 10% በባንክ የተረጋገጠ የባንክ ዋስትና (Unconditional Bank Guarantee) ማቅረብ የሚችል።
- ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ25 ተከታታይ ቀናት ውስጥ የማይመለስ ብር 50 /ሃምሳ ብር/ ብቻ በመክፈል የጨረታ ሰነድ ከሙ/ከ/አስ/ር ፋይናንስ ጽ/ቤት ቁጥር 3 ቀርበው መግዛት ይችላሉ፡፡
- ተጫራቾች በጨረታ ሠነድ ላይ በቀረበው ዝርዝር መሠረት ዋጋውን ያለምንም ስርዝ ድልዝ በአሃዝና በፊደል በመሙላት በሰም በታሸገ ፖስታ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሣጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡ ጨረታው በ25ኛው ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በስራ ቀን 6፡30 ተሽጎ በዕለቱ 8፡30 ሰዓት ላይ ይከፈታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-**

- መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
- ህጋዊ ተጫራቾችና ወኪሎቻቸው ባይገኙም በዕለቱ ጨረታው የሚከፈት መሆኑን እንገልጻለን፡፡
- ለበለጠ መረጃ ስልክ፡-09-12-04-86-80 መጠቀም ይቻላል፡፡

**በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ከ/ጠ/ዞን የሙዱሳ ከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤት**